# ድሬ

19ኛ ዓመት | ቁጥር 872 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ | ሚይዚያ / 16 / 2016 ዓ.ም



የዝናቡን መዝነብ ተከትሎ የሽንት ቤት ፍሳሽ መልቀቅ እና የታቆሩ ውሃዎችን አለማፋሰስና አለማዳረቅ ለአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት/አተት እንዲሁም ለደንጊና ለወባ ተጋላጭ ስለሚያደርግ የታቆሩ ውሃዎችን በማፋሰስና በማዳረቅ እንዲሁም በምንም ምክኒያት የሽንት ቤት ፍሳሽ ባለመልቀቅ የራሳችንንም ሆነ የሌሎችን ጤና እንጠብቅ።

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ


# "ብቃት" የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ሁለተኛ ዙር የህይወት ክህሎት ስልጠና ያጠናቀቁ 2 ሺ ሰልጣኞች ተመረቁ

የድሬዳዋ አስተዳደር የሥራ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ “ብቃት” የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት ሁለተኛ ዙር የህይወት ክህሎት ስልጠና ያጠናቀቁ 2 ሺ ሰልጣኞች የምርቃት መርሃ-ግብር በድምቀት ተካሂዷል፡፡

በዚህ የሰልጣኞች የምርቃት ፕሮግራም ላይ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ ፣ኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ ክቡር ሀርቢ ቡህ በመገኘት ለተመራቂዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

አቶ ሀርቢ ተመራቂዎችን በቀጣይ በተለያዩ ፋብሪካዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ በምትቀላቀሉበት ወቅት በስነ-ምግባር የታነፃችሁና በታታሪነት የምታገለግሉ መሆን ይገባቹሀል በማለት የመከሩ ሲሆን፤ ለዚህ መርሀ ግብር መሳካትም አስታዎፆ ላበረከቱ አካላት ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር የስራ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሮቤል ጌታቸው በበኩላቸው ለተመራቂዎች እንኳን ደስ አላችሁ በማለት በስልጠናው ወቅት ያሳዩትን የስራ ተነሳሽነትና ስነ-ምግባር በቀጣይም እንዲያጠናክሩት ተናግረዋል።

በተለይም አሁን ላይ በድሬዳዋ ኢንደስትሪ እየተስፋፋ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወጣቱም አስፈላጊውን ስነ-ምግባርና ክህሎት አግኝቶ ዘርፉን እንዲቀላቀል እንደነዚህ አይነት



ስልጠናዎች ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው የገለፁት ደግሞ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታ የሆኑት አቶ ዳንኤል ተሬሳ ናቸው።

አቶ ዳንኤል አያይዘውም ብቃት የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ የወጣት ስራ አጦችን ቁጥር በመቀነሱ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመዋል።

ተመራቂዎች በበኩላቸው በስልጠና ቆይታቸው በርካታ ክህሎት እንዳገኙ ገልፀው ለስልጠናው አዘጋጆችም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

**በኤደን ሳሙኤል**

**ፎቶ:- ሙሉዓለም ደሴ**

# የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አበረታች ውጤት እያመጡ እንደሚገኙ ተገለፀ



በድሬዳዋ አስተዳደሩ የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት እየተሰሩ ያሉ ስራዎች አበረታች ውጤት እያመጡ እንደሚገኙ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፍስሃ ይታገሱ ገለፁ።

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ልዑክ ቡድን በድሬዳዋ አስተዳደር ከዋጋ መረጋጋት ጋር በተያያዘ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ተዘዋውረው ተመልክተዋል።

በጉብኝቱም እለት እንደተገለፀው መንግስት ከቀረጥ ነፃ በመፍቀድ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎችን በፍራንኮ ቫሉታ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው የጅምላ አከፋፋይ ነጋዴዎችን የስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ በሚኒስትር ዴኤታው በተመራው ልዑኳን ቡድን ተዘዋውረው ተጎብኝተዋል።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# በዲያስፖራ የኢንቨስትመንት እና የቤት ልማት ፓኬጅ ቀረፃ ዙሪያ ምክክር ተካሄደ



በድሬዳዋ አስተዳደር በንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በዲያስፖራ የኢንቨስትመንት እና የቤት ልማት ፓኬጅ ቀረፃ ዙሪያ ከእስትሪንግ ኮሚቴና ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል ።

በዚሁም መርሀ-ግብር ላይም በመገኘት ንግግር ያደረጉት የድሬዳዋ አስተዳደር ምክትል ከንቲባና የንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ሀላፊ አቶ ሀርቢ ቡህ በተለይም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ ዲያስፖራዎች በሀገራቸው ልማት ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በርካታ ስራዎች እየተሰራ መሆኑን ተናግረው፤ በድሬዳዋ አስተዳደር ላይም ባለፉት ሁለት አመታት ዲያስፖራዎችን አሳታፊ የሚያደርገውን ናፍቆት የድሬዳዋ ሳምንትን በማዘጋጀት በርካታ የድሬዳዋ ተወላጆች

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# የኦቲዝም ግንዛቤ ማስጨበጫ ወርን አስመልክቶ በድሬዳዋ ታላቅ የእግር ጉዞ ፕሮግራም ተደረገ



በዚህም ከማለዳ ጀምሮ በማርሽ ባንድ በታጀበው የእግር ጉዞ መዳረሻም የለገሀሬ አካባቢ ነዋሪዎች ለእግር ጉዞው አስተባባሪዎችና ተሳታፊዎች፣ በኦቲዝም ጥላ ስር ለሚገኙ ልጆች እንዲሁም ለወላጆች ደማቅ አቀባበል አድርገውላቸዋል።

በመርሀ-ግብሩ ላይ በኦቲዝም ጥላ ስር ያሉ ልጆችን ቤት ከማዋል ይልቅ ከማህበረሰቡ ጋር በመቀላቀልና በማስተማር ለውጥ እንደሚመጣ የሚያመላክቱ ባነሮች በስፋት ታይተዋል።

**በኤደን ሳሙኤል**

**ፎቶ:- ሙሉዓለም ደሴ**

# በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት የፓርቲ ሥራዎች በቅንጅት በመመራታቸው ዘርፈ-ብዙ ውጤቶችን ማስመዝገብ መቻሉን የብልፅግና ፓርቲ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት አስታወቀ

የብልፅግና ፓርቲ የድሬዳዋ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የፓርቲ ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት የግምገማ መድረክ ተካሂዷል። በግምገማ መድረኩ ላይ የቅ/ጽ/ቤቱ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት የፓርቲ ሥራዎችን በቅንጅት በመምራት በዋናነትም የአስተዳደሩን ሠላም የማስጠበቅና የማዝለቅ: የሌማት ትሩፋት ተግባራትና ሌሎችም ዘርፎች በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲፈፀሙ አመራር በመስጠትና ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አመርቂ ውጤት መመዝገቡ በሪፖርቱ ተመላክቷል።

የህዝብ ግንኙነት ዘርፍን የስራ አፈፃፀም በማሳደግም የብልፅግና ዕሳቤ በኅብረተሰቡ ውስጥ ገዥ እንዲሆንና በማኅበረሰቡ ውስጥ ወንድማማችነትና እህትማማችነትን የማጎልበት መጠነ-ሰፊ ስራዎች መሠራታቸውም በመድረኩ ተገልጿል።

በመድረኩ ላይ የሴክተር ተቋማት: የወረዳና የገጠር አደረጃጀቶች የዘጠኝ ወር አፈፃፀማቸውን አቅርበው ባቀረቡት ላይ አስተያየትና ግብረመልስ ተሰጥቷቸዋል።

የብልፅግና ፓርቲ የድሬዳዋ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ምክትልና የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሻኪር አህመድ ከተፎካካሪ ፓርቲዎችና ከሲቪክ ማህበራት ጋር በቅርበትና በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ የገለፁ




ሲሆን በልማትና በበጎ አድራጎት ሥራዎች የሲቪክ ማህበራት በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች በመስጠት አባላትን የማብቃት ሥራዎች እንደሚሰራም አቶ ኢብራሂም ገልፀዋል።

የፓርቲና ሥራን ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይገባል። ኃላፊው የህዝቡን የሠላምና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች መመለስ ተቀዳሚ ተግባር በመሆኑ በዚህ ረገድ በከፍተኛ ትጋትና ቁርጠኝነት መሥራት እንደሚያስፈልግ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

የብልፅግና ፓርቲ ድሬዳዋ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ደረጀ ፀጋዬ በበኩላቸው ለሀገረ መንግሥት ምሥረታ ምሰሶ ጠንካራ ተቋማት መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን ጠንካራ ተቋማት እንዲፈጠሩ መሥራት አለብን ብለዋል።

በቀጣይም አዎንታዊ የሆነ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር በውጤትና በአፈፃፀም የሚለካ ዕውቅና የመስጠት ስራዎች እንደሚሰሩም አመላክተዋል።

በመጨረሻም የብልፅግና ፓርቲ ድሬዳዋ አስተዳደር ቅጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ኢብራሂም ዩሱፍ

በየደረጃው ያሉ የብልፅግና ፓርቲ መዋቅሮች በጥናት ላይ በመመሥረት በመዋጮ የሚሰበስቡትን ሀብት ለማሳደግ በቀጣይ መስራት እንዳለባቸውና የራሳቸው የሆነ ቢሮ እንዲኖራቸው ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ አቅጣጫ ሰጥተዋል።

የብልፅግና ፓርቲ አባላትን ቁጥር ለማሳደግ መሠራት እንዳለበት የጠቆሙት የብልፅግና ፓርቲ የድሬዳዋ አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊው አቶ ኢብራሂም ዩሱፍ ጥራት ያለው አባል ለማፍራት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በመድረኩ ላይ የብልፅግና ፓርቲ የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የስራ ሃላፊዎች እንዲሁም ከሴክተር: ከወረዳና ከገጠር የተውጣጡ የብልፅግና ፓርቲ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።

# በድሬዳዋ አስተዳደር ዘርፈ-ብዙ የህክምና አገልግሎቶችን ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን የፈረንሳይ የህክምና ቡድን ገለፀ



ፕሮፌሰር ፈርሂ የተመራው የህክምና ቡድን የህክምና አገልግሎቶችን መስጠት በሚችልበት ሁኔታ ላይ ከድሬዳዋ አስተዳደር ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ጋር ምክክር አካሂዷል።

የህክምና ቡድኑን ተቀብለው ያነጋገሩት የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ገበየሁ ጥላሁን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ኢትዮጵያና ፈረንሳይ የቆየና ጠንካራ የሆነ ግንኙነት እንዳላቸው ጠቅሰው የህክምና ቡድኑ በድሬዳዋ አስተዳደር ዘርፈ-ብዙ የህክምና አገልግሎቶችን ለመስጠት በመምጣቱ ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

የህክምና ቡድኑ ለአስተዳደሩ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀው የድሬዳዋ አስተዳደር ለህክምና ቡድኑ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ አቶ ገበየሁ በንግግራቸው አረጋግጠዋል።

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ፀጌረዳ ክፍሌ በበኩላቸው የህክምና ክፍተት ባለበት የቀዶ ጥገና ዘርፍ በድሬዳዋ አስተዳደር የህክምና አገልግሎት ለመስጠት የመጣውን የህክምና ቡድን ተቀብለው ያነጋገሩ ሲሆን የህክምና ክፍተት ባለበት የህፃናት ቀዶ ጥገና: የልብ ቀዶ ጥገናና የነርቭ ቀዶ ጥገና ዘርፍ ላይ ሙያዊና ባለሙያዎችን የማሰልጠን ድጋፍ እንዲደረግላቸው እንዲሁም በህክምና ግብዓትና መሠረተልማት በማሟላትም የህክምና ቡድኑ ዕገዛ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

የህክምና ቡድኑ መሪ ፕሮፌሰር ፈርሂ በድሬዳዋ አስተዳደር በተደረገላቸው አቀባበል ደስተኛ መሆናቸውን ገልፀው በአስተዳደሩ ዘርፈ-ብዙ የህክምና አገልግሎቶችን ለመስጠት ቡድናቸው ዝግጁ መሆኑን ገልፀዋል። የህክምና ቡድኑ በተለያዩ የቀዶ ጥገና የህክምና ዘርፎች ህክምና የመስጠት: ባለሙያዎችን የማሰልጠንና በግብዓትም ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልፀዋል።

የህክምና ቡድኑ ከድሬዳዋ ዩኒቨርስቲና ከሌሎችም የህክምና ባለሙያዎች ጋር ውይይት ያደረገ ሲሆን የፈረንሳይ ሆስፒታልና በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማራውን ብራ ኮፊንም ተዘዋውረው ጎብኝተዋል።

የህክምና ቡድኑ በቀጣይ ህዳር ወር በመምጣት የህክምና አገልግሎቱን እንደሚሰጥ ለማወቅ ተችሏል።

**/በሄኖክ ይልማ/**

# "የብልፅግና ትሩፋት የሆነውን የመንገድ መሠረተ ልማት ለማህበረሰባችን ተደራሽ ለማድረግ በመስራት ላይ ነን፡፡"

**ኢንጂነር ያሲን አህመድ ሙሳ**

የበኬ ሀሎ የገጠር መንገድ በአካባቢው ድንጋያማ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት ለትራንስፖርት እንቅስቃሴ አመቺ ስላልነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ያነሱት የነበረውን ቅሬታ ለመፍታት የድሬዳዋ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን መንገዱን በማስጠገን ላይ ይገኛል፡፡

17 ኪ.ሜ የሚሸፍነውና ግንባታው ከተጀመረ ሁለት ሳምንት የሆነው ይህ የገጠር መንገድ በዋነኝነት ገንደ ገበሬ፣ ለገዶን፣ በኬ ሀሎ፣ ቢሻን በሄ እና ቃልቻ የገጠር ወረዳዎችን ከማገናኘቱ ባሻገር የአዋሌና የአሰሊሶ ክላስተሮችን የሚያገናኝ በመሆኑ መንገዱ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅምና ትስስር የሚፈጥር ነው ሲሉ በድሬዳዋ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ግንባታ፣ ጥገና፣ ቁጥጥርና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ኢንጂነር ያሲን አህመድ ሙሳ ገልፀውልናል፡፡

በተለይም አካባቢው የከርሰ ምድር ውኃ ባለቤት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወረዳዎቹ ከፍተኛ የግብርና ምርት አምራች ስለሆኑ የመንገዱ መጠገን አርሶ አደሩ ያመረተውን የግብርና ምርት በቀላሉ ወደ ገበያ አውጥቶ መሸጥ ስለሚያስችለው መንገዱ ለአካባቢው ነዋሪዎች ብሎም ለአስተዳደሩ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አለው ሲሉ ኢንጂነር ያሲን አህመድ ተናግረዋል፡፡

የአስተዳደሩ መንገዶች ባለስልጣን በ5 ሚሊየን ብር በጀት እያስገነባ ያለው ይህ የገጠር መንገድ ለረጅም ግዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ታቅዶ በመሰራት ላይ እንደሆነና በቀጣይ የውኃ መውረጃ ቦዩችም ጭምር ያካተተ ግንባታ እንደሚሰራለት ኢንጂነር ያሲን አህመድ አክለው ገልፀዋል፡፡

የመንገድ ስራው የሚሰራበት አካባቢ ዐለታማ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ስራውን ፈታኝ ቢያደርገውም በተቋራጭ ድርጅቱ ጠንካራና ብቁ የሰው ኃይል እንዲሁም የተሟላ ማሽነሪ በመታገዝ ፕሮጀክቱን በተያዘለት የግዜ ገደብ ሰርቶ ለማስረከብ ቀንና ማታ በመስራት ላይ መሆናቸውን ኢንጂነር ታምራት ታደሰ የታምራት ታደሰ ጠቅላላ ተቋራጭ ስራ አስኪያጅ



ገልፀውልናል፡፡

የመንገድ ስራውን ከሁለት ሳምንት በኃላ አጠናቀው ለማስረከብ በመስራት ላይ መሆናቸውን የገለፁልን ኢንጂነር ታምራት ታደሰ በተለይም ለመንገዱ በፍጥነት መገንባት ምክንያት የሆነው የአካባቢው ነዋሪ ዘወትር ከጎናችን በመሆን አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላትም ጭምር እያበረታታንና እያገዘን ይገኛል ሲሉም ኢንጂነር ታምራት ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር በመሆን በሰሯቸው ሩቁ ቁልቢ፣ አሙማ፣ አዳዳ ቁጥር ሁለትና ቢያዋሌ ቃልቻ የገጠር መንገድ ልምዶች ይህንንም ፕሮጀክት በአጭር ግዜ ሰርተው ለማጠናቀቅና ለማስረከብ በመስራት ላይ መሆናቸውን ኢንጂነር ታምራት ታደሰ ገልፀዉልናል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረው መንገድ እንደልብ በትራንስፖርት መንቀሳቀስ ይቸገሩ እንደነበር ያወሱት የአካባቢው ነዋሪዎች አሁን መንገዱ በመጠገኑ እጅግ ደስተኛ መሆናቸውንና ያመረቱትንም የግብርና ምርት በቀላሉ ወደ ገበያ አውጥተው

መሸጥ እንደሚችሉ በመግለፅ መንግስት ችግራቸውን አይቶ መንገዱን እያስጠገነላቸው በመሆኑ አመስግነዋል ሲል የዘገበው የተቋሙ ህዝብ ግንኙነት ክፍል ነው፡፡

# ርዕሰ - አንቀጽ

## ፀረ ሠላም ኃሎችን ከብሄርና ከሐይማኖት ተቋማት ልንለያቸው ይገባል ! ! !

ከብዙ ድካም እና ልፋት በኋላ ከበርካታ ዓመታት ቀጥሎ የብሄር ብሄረሰቦች፣ የሐይማኖቶች እና የሌሎችም ልዩነቶች የእኩልነት ጥያቄ በአካታች እና አሳታፊነት ከተመለሰ በኋላ እንኳን ልዩነቶቹን እንደ መደበቂያ ምሽግ የመጠቀም ስትራቴጂ አሁንም ይታያል፡፡ በተለይ ያኮረፉ ፖለቲከኞች፣ ኪራይ ሰብሳቢዎች፣ ሽብርተኞችና ሌሎችም ጸረ ሠላም ኃይሎች ለሁሉም ዜጎች የተዘረጋው ሠላማዊውና ህጋዊው መንገድ አላዋጣ ሲላቸው ህገ ወጡን መንገድ ለመጠቀም ልዩነቶችን እንደ ምሽግ የሚመስል ካባ በመልበስ በዋነናነት የሚጠቀሙት ሐይማኖትንና ብሄርን ነው፡፡

ይህን አካሄዳቸውን አደገኛ የሚያደርገው ሐይማኖትን ከሐይማኖት፤ ብሄርን ከብሄር በማጋጨት ይህች ሀገር ማባሪያ ወደሌለው ትርምስ ውስጥ እንድትገባ ስለሚያደርግ ነው፡፡ በሐይማኖቶችና በብሄሮች መካከል የሚነሳ ግጭት ደግሞ ከራሳችንም ሆነ ከዓለማችን ታሪክ እንደምንረዳው አሸናፊና ተሸናፊ የሌለው እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ የሚሄድ አደገኛ ነገር ነው፡፡

እነዚህ ራስ ወዳድ የጥፋት ኃይሎች ሲመቻቸው የሐይማኖት ተቆርቋሪ በመምሰልና በለውጡ ሥርዓት የተመለሰውን ጥያቄ እንዳልተመለሰ በመስበክ በርካቶችን በስሜታዊነት በእሳት እንዲማግዱ አድርገዋል፡፡ በዚህ አልሳካ ሲላቸው ደግሞ የአንዱ ብሄር ተቆርቋሪ በመምሰልና ሌላውን በመኮነን የዋሆችን ለእኩይ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ በማድረግ ለዚህች ሀገር ብዙ መልካም ነገር ማድረግ የሚችሉ ዜጎችን በከንቱ እንዲሞቱ አድርገዋል፡፡

አዲሱ የለውጥ ጉዟችን የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ለበጎ ተግባር ከማዋል ይልቅ ለዚሁ እኩይ ተግባራቸው እየተጠቀሙበት በሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች ግጭትና ሁከት እንዲፈጠር አጥብቀው እየሠሩ ናቸው፡፡ በዚህም መንግስትን ከህዝብ በማቃያየም ለህዝብና መንግስት አላስፈላጊ የሆነ የቤት ሥራ በመፍጠር ለራሳቸው ግን ዕድሜያቸውን የሚያራዝሙበትን ዕድል ሊያመቻቹ ያስባሉ፡፡

ይህ ከንቱ ምኞታቸው እንዳይሳካ የዕምነት አባቶች፣ አባ ገዳዎች፣ ኡጋሶች እና የአገር ሽማግሌዎች የማይተካ እና ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ የሚመከረውን በመምከር፣ የሚወቀሰውን እና የሚገሰጸውን በመገሰጽ እንዲሁም የሚቀጣውን በመቅጣት የተያዙትን የሠላም ሥራ አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

ክቡር ከንቲባችን እና ሌሎችም ከፍተኛ አመራሮች የሚያደርጉት የውይይት መድረክ በእነሱ ምርቃት መጀመሩ ከፈጣሪ ጋር ያለንን ግንኙነት የሚያጠናክር ነው፡፡ ለሠላማችን፣ ለዝናቡ እና ሌሎችም በጎ ነገሮች በመጸለያቸው ይህን በተግባር እያየነው ነው፡፡

የዘንድሮው ጾም በጋራ መጀመሩ እና ዓመት በዓላትን በጋራ ማድረጋችን መቼም የማይረሳና ለሌላም ወቅት አርዓያ ነው፡፡ ለተከበረው ዓመት በዓል ረመዳን ከሪም ብለናል፤ ቀጣዩ በዓል ደግሞ ሲመጣ በተመሳሳይ በቡራኬ ሊሆን ይገባል፡፡

# አጀንዳ

## ነጩ እና ጥቁሩ የዓይነ - ስውርነቶች

በዓለም ላይ በከፍተኛ መጠን ዓይነ-ስውርነቶች ከሚያስከትሉ ምክንያቶች ሁለቱ ቀዳሚዎቹ ነጩ እና ጥቁሩ ዓይነ-ስውርነቶች በመባል ይታወቃሉ፡፡

ነጩ - ሞራ ግርዶሽ

ሌንስ፡- የዓይን ፊተኛዉ ክፍል ዉስጥ ያለ ንዑስ-ዓይን አካል ሲሆን - በተፈጥሮዉ ጥርት ያለ ነዉ፡፡ ስራዉ ብርሃንን ወደ ኃለኛዉ የዓይን ክፍል - የብርሃን ግድግዳ(ረቲና) - መርቶ ማስተላለፍ አንዱ ነዉ፡፡

ሞራ ግርዶሽ፡- ሌንስ ጥራቱን በተለያዩ ምክንያት ሲያጣ - በተለያየ መጠን ወደ ነጭነት ሲቀየር እና ዋናዉ አገልግሎቱ ሲታወክ - ሞራ ግርዶሽ ተከሰተ ይባላል፡፡ ይህ ዓይነ-ስዎርነትን ከሚያመጡ ምክንያቶች በዓለም ላይ በአንደኛ ደረጃ ይቀመጣል ፡ ይህም ከግማሽ በላይ ይይዛል፡፡ ሞራ ግርዶሽ አብዛኛዉ ከእድሜ ጋር ተያይዞ የሚከሰት ሲሆን ሌላው ደግሞ ከእድሜ መግፋት ጋር ያልተያያዘ ነዉ፤ በብዙ ምክንያት ሊመጣ ይችላል ፡ ለምሳሌ .. ከግርዶሹ ጋር አብሮ በመወለድ(ብዙ ምክንያቶች አሉት)፣ በምት ፣ እስቴሮይድ መድሃኒት ከመጠቀም ጋር የተየያዘ፣ በዉስጣዊ የዓይን ቁጣ፣... ወዘተ

ሆኖም ይህ የሞራ ግርዶሽ በቀዶ-ጥገና የሚግላገሉት የዓይነ-ስዉርነት ምክንያት ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ከጥቁሩ - ግላኮማ ይልቅ ነጩ-ሞራ ግርዶሽ ለታማሚዉም ለሀኪሙም ቀዶ-ጥገና ከተከናወነ በኃላ ትልቅ የእርካታ እና የደስታ ምንጭ ነዉ፡፡ የሀዘን እና የብስጭት ምንጭ የሚሆነዉ ሞራ-ግርዶሹ ተጉዳኝ የዓይነ-ስዉርንት የሚያመጣ ምክንያት ካለዉ/ካሉት ነዉ....አንዱም ያ..ጥቁር-ግላኮማ ሊሆን ይችላል፡፡

ጥቁሩ - ግላኮማ

የዓይን ነርቭ፡- የዓይን ህዋሳት ከብርሀን ግድግዳ (ረቲና) ተሰባስበዉ ህብረ-ህዋስ ፈጥረዉ በኃለኛዉ የዓይን ክፍል ወደ አንጎል የሚጉህዙበት ገመድ ነዉ፡ ፡ ስራዉም ብርሃንን እና ያየነዉን ምስል/እንቅስቃሴ በነርቭኛ ተርጉሞ ወደ እይታ-አንጎል ክፍል መማስተላላፍ ነዉ፡፡

ግላኮማ፡- የአይን ነርቭ መጎዳት ሲሆን ፤ የዓይናችን ነርቭ ጉዳት ለመገንዝብ ያህል በግላኮማ ምክንያት እና በሌላ ምክንያት ብለን መክፈል እንችላልን፡፡ ግላኮማ - በጊዜ ሂደት ጉዳቱ የሚጨምር ፣ የማይድን ግን የሚታከም የራሱ አይነተኛ አጎዳድ ያለዉ፤ የራሱ አይነተኛ የዓይን -አድማስ እክል የሚያምጣ ነዉ፡፡ ለግላኮማ አጋላጭ ከሆኑት ዉስጥ ዋናው ከፍተኛ የዓይን ግፊት (ከ 21 ሚሜ.ሜር በላይ) ሲሆን ፤ ነገር ግን የግድ ከፍተኛ ግፊት ላይኖር ይችላል፡፡

ብዙ አይነት ግላኮማ አለ... በመንስኤዉ - የሚታወቅ እና የማይታወቅ፣ በእድሜ - የህጻናት ፡ የወጣቶች እና የአዋቂዎቸ፤ በማዕዘኑ(የዓይን ፈሳሽ የሚፈስበት ቦይ)- ማዕዘነ ክፍት እና ማዕዘነ-ዝግ... ተብሎ በዋናነት ይከፍላል፡፡

የህጻናት ገላኮማ፡- ከ4 ዓመት በታች ያለዉን እድሜ ክልል የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ከሌላዉ ዕድሜ የሚለየው አልፎ አልፎ የሚከሰት መሆኑ፤ ሁሌም ክፍተኛ የዓይን ግፊት መኖሩ፣ ጉዳቱ የዓይን ነርቭ ላይ ብቻ ሳሆን ሁሉም እድገታቸዉን ያልጨረሱ የዓይን ክፍሎች ላይ መሆኑ፤ ጠቁሮ ያልጠቆረ...የሚታይ ምልክቶች ማለትም ሶስትዮሽ መገለጫ ያለዉ ...ማንባት፡ ብርሃን መፍራት እና የዓይን ቆብን መጭመቅ፡፡ ህክማናዉም የዓይኑን ግፊት በቀዶ-ጥግና መቀነስ ነዉ፡፡ ጉዳቱ እንዳይቀጥል ማድረግ ነዉ ህክምናዉ....የደረሰዉ ተጎዳ አይምለስም፡፡

የወጣቶች እና አዋቂዎች ግላኮማ፡- እነዚህ በጥቁር የሚመሰሉት ... ሲጀመሩ ምንም ምልክት የማያሳዩ፤ በጭለማ እንደሚዘርፍ ልባ ... ከፍተኛ ጉዳት ካመጡ በኃላ ነዉ የሚታወቁት ምክንቱም የዓይን እይታን መጀመርያ ኣከባቢ ምንም አቀንሱም፡፡ የአይን አድማስ በከፍተኛ ሁኔታ ጠቦ ከነገሮች ጋር ስንጋጭ ወይም ዓይነ-ስዉርት ሲክስተ ነዉ የሚታወቀዉ... ይህ እንግዲህ በዓለም ከነጩ-ሞራ ግርዶሽ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ዓይን-ስዉርነትን ከሚያመጣዉ የማዕዘነ-ክፍት ግላኮማ አይነት መገለጫ ነዉ፡፡

ይህም ዕድሜያቸዉ ከ40 ዓመት በላይ ተጋላጭ ሲሆኑ....ዕድሜ በጨመረ ቁጥር ተጋላጭነትም ይጭምራል፡፡ ለዚህም ሲባል በዚህ ዕድሜ ክልል ዉስጥ ያለ ሰዉ ቢያንስ አንዴ የዓይን ምርመራ ማድረግ ይመከራል፡፡ ተጨማሪ ተጋላጭነት ያላቸዉ ሰዎች ለምሳሌ የቅርብ ቤተሰብ አባል በግላኮማ የተጠቃ ካለ....የቅርብ ክትትል ያሰፈልጋቸዋል፡፡ ወደ ህክምናዉ ስንመጣ ብቸኛዉ ማከሚያዉ (የማይድን ነዉ ብለናል) መንገድ የዓይን ግፊቱን ካለበት መነሻ መቀነስ ነዉ፡፡ ይህም ጉዳቱን ባለበት ማቆም ወይም ዓይነ-ስውርነትን እንዳይከሰት ማቆየት ነው፡፡ ግፊቱን ካለበት ለማዉረድ ሶስት ዓይነት ህክመና አማራጮች አሉት....እናሱም የአይን ጠብታ፣ ጨረር እና ቀዶ-ህክምና ናቸዉ፡፡

ነጩም ይዳን፤ ጥቁሩም ይታከም!

ብርሃኖን ይጠብቁ፡፡

የድሬዳዋ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በየሳምንቱ የሚታተም **ሚያዚያ 21/1996 ዓ.ም** ተጀመረ

ረቡዕ - ሚይዚያ / 16 / 2016 ዓ.ም

ድሬ ጋዜጣ

**አዘጋጆች**
በድሉ ኃይሌ
ማቲያስ አንዳለ
እስከንድር ኡስማን
ዳንኤል አማረ

**ፎቶ ግራፈር**
ሰላም አበበ

**ዋና አዘጋጅ**
ሔለን ሽጉጤ
( 09 20 26 49 55 )

**ሌይአውት ዲዛይን**
ሰማን ሙስጠፋ

**የኮምፒዩተር ፅሁፍ**
አለም አስጨናቂ

ስልክ - 025 111 6065
ፋክስ - 025 111 4972 ፖ.ሳ.ቁ 370
ኢ-ሜይል - Info pubbure@yahoo.com
ዌብሳይት - www.direcomm.gov.et
ፌስቡክ - Dire Dawa Geovernement Communication Affairs Bureau (@DDGCAB)

# ያልተገራው የማህበራዊ ድረ - ገፅ አጠቃቀማችን

በስንታየሁ እንግዳ



ህዝበ አዳም ያኔ ያኔ ሩቅ ካለ ወዳጁ የሆድ የሆዱን ለመጨዋወት የሚጠቀምባቸው ጥቂት የግንኙነት ዘዴዎች የነበሩት ሲሆን እንዚህ የግንኙነት ዘዴዎች አንድም በአካል አሊያም በስማ በለው በመልዕክተኛ እንደነበር ድርሳናትና እራሳቸው አበው በአንደበታቸው የሚመሰክሩት ነው፡፡ ጊዜ ጊዜን እየተካ የሰዎችም የዕውቀት ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሄድ ወራትን በፈጀ ጉዞ ከልብ ወዳጅ አሊያም ከዘመድ አዝማድ ተገናኝቶ ለማውጋት የሚፈጀውን ጊዜ ለማጥበብና የልብን ሀሳብ ለማስተላለፍ የግድ በአካል መገናኘት ሳያስፈልግ እንደነ ፖስታና ቴሌግራምን የመሳሰሉ የግንኙነት መስመሮች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ፡፡ በመቃ ዘንግ ላይ የተሰካ ፖስታ ምስል በየፖስታ ቤት ደጃፍ ላይ ስንመለከት የያኔውን የመገናኛ ቴክኖሎጂ ዘግመተኛ ለውጥ ማሰባችን አይቀርም፡፡

ብዙም እሩቅ ሳንሄድ በጣት በሚቆጠሩ ዓመታቶች ስንቶቻችን ለወዳጅ ዘመዶቻችን ካለንበት ሆነን ቴንብር በተለጠፈበት ፖስታ መልዕክቶችን ተላልከን ይሆን? ደሞስ ስንቶቻችን አይደልም ሩቅ ላለ ዘመድ ወዳጅ እዛው ምናልባትም ካፍ አፍንጫ ለማይርቁን ተፈቃሪዎቻችን ዳርዳሩ በአበባ በተንቆጠቆጠ በቀይ ቀለም መሀሉ በጦር በተወጋና በልቡ ውስጥ ያለው ደም ከፍቅር የተነሳ ፈሶ ፈሶ ዕሩብ ያህሉ መቅረቱን በሚያሳይ መልኩ ጦሩ ሳይነቀል ወረቀት ላይ በተሳለ ስዕል የታጀበ የፍቅር ደብዳቤ ውድና ውብ በምንላቸው አረፍተ ነገሮች እንደየ ቋንቋችን ከትበን ባገኘነው ዘዴ በፖስታ አሽገን ላፈቀርነው ሰው አቃብለን ይሆን?፡፡

ትናንት እንደዛ የታለፈው ዛሬ ላይ ለመድረስ መሆኑ ለሁላችንም የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ እናስ ዛሬ ምን ተኮነ? ብላችሁ ለምትጠይቁኝ ዛሬማ ዓለም በቴክኖሎጂ ማዕበል እየተናጠች፤ በየ ደቂቃዎች ከአራቱም አቅጣጫ የአዳዲስ ግኝቶችን ዜና እየሰማች፤ ደሞም አንዱን ግኝት ሽራ ሌላውን ሳይውል ሳያድር እየተካች ተጠጋግታ ተጠጋግታ ወደ አንድ መንደርነት መጥታለች፡፡ የዚህ ሁሉ በሰኮንዶች ውስጥ ሰሜን ጫፍ የተደረገው ደቡብ ጫፍ ከመቅፅበት መሰማት መታየቱ፤ የምስራቁ ጥግ ለምዕራቡ የቡና አጣጭ ዓይነት ጎረቤት የመቀራረቡ ሚስጥር ዘመን ያፈራቸው የመገናኛ አውታሮች ውጤት መሆኑን ለአንድ አፍታም ለመዘንጋት መሞከር ውለታቢስነት ነው ብልስ?፡፡

በየጓዳቸው በራቸውን በራሳቸው ላይ ዘግተው ከፈጠነው በላይ ፈጥነን እንድንገናኝ የሚተጉልን የፈጠራ ሰዎች በየጊዜው እያሻሻሉ የሚያወጧቸው የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች በመዳፎቻችን መሀል አድርገናት ዓለምን እንድንፈትሻት አስችሎናል፡፡ ዓለም አንድ መንደር ናት / The world is a Global Village / እንዲሏት ፈረንጆቹ ዘመናዊዋ ዓለም ከብዙው ህዝቧ አብዛኛውን በቴክኖሎጂ ጠበሏ አጥምቃ ግዞተኛዋ አድርጋለች፡፡ በተለይ በተለይ ከዘመናዊ የግንኙነት መረቦች ውስጥ ኢንተርኔትን በመጀመሪያው ረድፍ ውስጥ አለማስቀመጥ ማለት ከስህተተኞች ጎራ የሚያሰልፍ ነው፡፡ ኢንተርኔት አንድ ሰው ከቤቱ ሳይወጣ ዓለምን የሚዞርበት፤ የትኛውም ስፍራ ላይ ስለተከሰተ ጥሩም ይሁን መጥፎ ጉዳይ መረጃ የሚያገኝበት፤ በማናቸውም ስፍራ ካለ ሰው ጋር ርቀት፣ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥና ተፈጥሮዋዊ መሰናከሎች ሳያግዱት በሰኮንዶች ውስጥ የሚገናኝበት የዘመናችን ድንቅ ፈጠራ ነው፡፡

ለብዙዎች የሰው ልጆች የደም ስርን ያህል ያስፈልጋል የሚባልለት የግንኙነት ስርዓት የተለያዩ ማህበራዊ ድህረ-ገፆች ተካተውበት በየትኛውም የምድር ጫፍ ያሉና እስከመፈጠራቸው የማይተዋወቁ ሰዎችን ጓደኛማቾች እንዲሆኑ በማስቻሉ ተወዳጅነቱ ዕለት ተዕለት እየጨመረና የተጠቃሚዎቹም ብዛት በቁጥር ከፍ እያለ ይገኛል፡፡ በተለይ ከማህበራዊ ድህረ-ገፆች አንዱን መርጠን እንጨዋወት ብንል በዋናነት ቶሎ ብሎ ድቅን የሚልብንና የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው ፌስ ቡክ (FACE BOOK) ወይም ሀሪፎቹ አጠር አድርገው ሲጠሩት FB የሚሉት ማህበራዊ ድረገፅ ነው፡፡ መቼም በፌስ ቡክ አቅጣጫ የሚወሩ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ እሙን ነው፡፡ ከነዚህም ጉዳዮች አንዱ በአስፈላጊነቱና አላስፈላጊነቱ ላይ አልፎ አልፎ ጎራ ተለይቶ ክርክሮች ሲፈጠሩ ይስተዋላል፡፡

ለዚህ ደግሞ ሰበቡ በርካታ ነው ሆኖም ግን ሰበቦቹ ደግም ጥሩም ይሁኑ መጥፎ ዞሮ ዞሮ ጣቶች ሁሉ የሚጠቁሙት ወደ ተጠቃሚው ወደ ሰው ልጅ እንጂ ወደ ድህረ-ገፁ ሊሆን አይችልም፡፡ አብዛኞቹ ዛሬ ጠቀሙን ጎዱን እያልን የምናመሰግናቸው አሊያም የምንኮንናቸው መገልገያዎቻችን በኛው አእምሮ እየታዘዙና በስሜት ህዋሶቻችን ወደ ተግባራዊነት እየተለወጡ ጥሩና መጥፎ ብለን እኛ በሁለት ጎራ የፈረጅነውን ግልጋሎቶቻቸውን እየሰጡን ይገኛሉ፡፡ እነዚሁ የኢንተርኔት ድረገፆች ስራችንን እንዳቀለሉልንና ለግንኙነታችን መሳለጥ የማይናቅ ድርሻ እንዳላቸው ሁሉ በተለይ አሁን አሁን ልባችንን ከሚያሳርፈው አገልግሎታቸው ይልቅ ደግሞ ዛሬ ምን ጉድ ይዘው ይወጡ ይሆን? እያልን በነጋ በጠባ የምንሰጋው ስጋት ግለቱ ጨምሯል፡፡

የኢንተርኔት አብዮት ከመፈንዳቱ ጋር ተከትለው የመጡት ማህበራዊ ድረ-ገፆች ለአጠቃቀም ምቹ፣ በቀላል ወጪ ልንጠቀማቸው የምንችላቸው፣ በአንድ ጊዜ በርካታ አማራጮች ያላቸው በመሆናቸው የዕለት ተዕለት ፍላጎታችን ሆነዋል፡፡ እንደውም በወጣው ቆየት ያለ መረጃ መሰረት በዓለማችን በኢንተርኔት በኩል ከምንጠቀምባቸው ድረ-ገፆች ውስጥ ፌስቡክ (FACEBOOK)፣ ቲክ ቶክ(Tik Tok) ትዊተር (twitter) የመሳሰሉትን የሚጠቀመው የሰው ቁጥር 1.1 ቢሊዮን በላይ ሊሆኑ እንደሚችሉም ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ በርግጥ በሀገራችን ያለው የኢንተርኔት ተጠቃሚም ይሁን የዓለም ዓቀፍ የማህበራዊ ድረ-ገፅ ተጠቃሚው መጠን ካለው የዓለም ሕዝብ ብዛት አንፃር ሲናበብ እምብዛም ነው፡፡

በተለይ በሀገራችን የሕዝቡ ቁጥር 120 ሚሊዮን አካባቢ መሆኑን ተከትሎ ፋና ብሮድካስት ሚያዚያ 28/2014 ዓ.ም ባወጣው ፅሁፍ 29.83 ሚሊየን የኢንተርኔት ተጠቃሚ መኖሩ ብዙም አያስጨበጭብም፡፡ ዘርፉ ካለው ጠቀሜታ አንፃር ድፍን የዓለም ሕዝብ ቢጠቀምበት እሰየው የሚያስብል እንጂ የሚከፋ ጉዳይ አልነበረም በተለይ ነገሮቻችንን ቀላል ከማድረግ አንፃር እንደኛ ታዳጊ ለሆኑ ሀገራት የሚሰጠው ጠቀሜታ የትየለሌ ነው፡፡ ሆኖም ግን የማህበራዊ ድረ-ገፆችን ባመሰገንበት አንደበታችን ምነው ባልተፈጠሩ የምንልበትን ጊዜና ሁኔታ ስንመለከት ደግሞ በመንታ መንገድ ላይ ቆመን ግራ እንጋባለን፡፡ አብዛኞቹ ነገሮች በዘመናዊው ዘመን ሰው ተጠንስሶ ካለመኖር ወደ መኖር ሲመጡ ዕለት ተዕለት አዳዲስ ነገሮችን ለሚፈልገው ህዝበ አዳም አንደ አዎንታዊ ነገር እንዲጨምሩለት እንጂ እራሳቸው ሌላ የችግር ምንጭ እንዲሆኑ እንዳልሆነ የፈጠራ ሰዎችና ተመራማሪዎች ቢጠየቁ ‹‹እንዴታ›› በማለት የሚመልሱት እንደሆነ እገምታለሁ፡፡

የሰዎችን የጉዞ ሂደት ለማፍጠን ታስበው የተሠሩ የአውሮፕላን ዲዛይኖች ቦንብ ጣይ ተደርገው ሲሻሻሉና ለሰው ልጅ ስጋት ሲሆኑ፤ ለኃይል አቅርቦት መዋል የሚገባቸው የኒኩለር ቅመሞች በአንድ ዞር በሚከፈቱ ቁልፎች ሀገርን ያክል ለማጥፋት ተቀባብለው አንዳንድ ሀገራትን ፍጥጫ ውስጥ ሲከቱ ወዘተ. ማየት የዓለም የቴክኖሎጂ ዕድገት ፍጥነትና አልፎ አልፎ የሚፈጥረው ስጋት መሳ ለመሳ ሲጓዙ በራሱ ሌላ ስጋት ነው፡፡ የቅርቡን የአረብ ሀገራት አብዮት የተመለከተ ለአብዮቱ መቀጣጠል የማህበራዊ ድረ-ገፆች ሚና ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበረ የሚዘነጋ አይመስለኝም፡፡

እንደው በማህበራዊ ድረ-ገፆች የሚገኙት ጠቀሜታዎች እንዳሉ ሆነው በነዛው በሚጠቅሙን ድረ-ገፆች ያጣናቸውና የምናጣቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ ለናንተው ለቀባሪዎቹ ለማርዳት ብሞክርስ? ለዘመናት የገነባናቸው የኛነታችን መገለጫና ጠቃሚ ባህሎቻችን በእጃችን ላይ ባሉ ስልኮች በምንጠቀማቸው ማህበራዊ ድረ-ገፆች አማካኝነት በሚለቀቁ የማይመጥኑንና እኛን የማይገልፁ ድርጊቶች ተመስጠን በተዘዋዋሪ ቀኝ ስንገዛ መመልከት ምን ያህል ሊያም እንደሚችል ባህሌን እና እሴቴን ያለ የሀገሬ ሰው ሊያውቀው ይችላል፡፡ ወዳጆቼ ቀኝ ላለመገዛት አባቶቻችን ያን ሁሉ ተጋድሎ የማድረጋቸው ሚስጥር የሀገሬ ሰው ባህልና ወጉ ተጠብቆ ይኖር ዘንድ እና ያልተበረዘና ያልተከለሰ እሴነቱን ለልጅ ልጆቻቸው ለማውረስ ነበር፡፡

ፊት ለፊት ከመድፍና ታንክ ጋር መጋፈጥ የሚያስከፍለውን ዋጋ የሚፈጥረውን ስሜት ለማወቅ ታሪክ ከማንበብ እልፍ ያለ እርምጃ እንደሚያፈስልገው እሙን ነው፡፡ ግን እነዚህ አባቶች ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው ጠላትን ከተደበቀበት ጉድጓድ እያወጡ ወየው እናቴ ያሰኙት በኢትዮጲያ ከርሰ ምድር ያለውን ማዕድንና ተራራ ሸንተረሩን ለማስከበር ብቻ ነው ብሎ መደምደም የዋህነት ነው፡፡ ይልቁኑ የነሱ ትግልና የመረረ ትንቅንቅ እኛና እኛ ብቻ ያሉንን የማንነታችን መገለጫ የሆኑ ባህላዊ እሴቶቻችንን ጠብቆ ለማቆየትም ጭምር እንጂ፡፡ አሁን አሁን ግን ዘመኑ ለመልካም እንድንጠቀምባቸው በተሰጡን ቴክኖሎጂዎች እኛው እራሳችን በፍቃዳችን የሌሎች ሀገሮችን ባህልና ወግ ቀኝ ተገዢዎች ሆነናል፡፡

የማህበራዊ ድረ-ገፆች የህዝቡን ትኩረት የመያዝ አቅም በመጠቀም ልቅ የሆኑ የወሲብ ንግድን በማስፋፋት የሀገራትን ባህል ሲያፈራርስ መመልከት ከጀመርን ቆየት ብለናል፡፡ በፌስ ቡክ ድረ-ገፅ ተዋውቀው፤ ተጠያይቀው፤ ተጋብተው የተፋቱትን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ ቀድሞ በምሽቶቻቸው ተሰብስበው የሚወያዩ ቤተሰቦች ዛሬ በየፊናቸው የመኮራረፍ ያህል በቤቱ ውስጥ ዝምታን በማስፈን ፌስ ቡክና ቲክ ቶክ (Tik Tok)ን መስኮት ይኮመኩማሉ፡፡ ውሎ እንዴት ነው? ይሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ወላጆች ለልጆች ክፉና ደጉን የሚያስተምሩበት የቆየ የቤተሰብ ውይይት ፕሮግራሞች በማህበራዊ ድረ-ገፅ ተተክቶ ሁሉም በፈቀደውና በየፊናው እቤቱ ተቀምጦ ከቤቱ ይነጉዳል፡፡

ከላይ ያየነው የኛና የኛ የሆኑ ባህሎቻችን እና እሴቶቻችንን ማጣታችንን ነው በማህበራዊ ድረ-ገፆች አማካኝት፡፡ አሁን አሁን የማህበራዊ ድረ-ገፆች ባህልንና ወጎቻችንን ይንዱልን ዘንድ ከመፍቀድም አልፈን ሀገራዊ ህልውናችንን ጭምር እንዳልነበር ያደርጉ ዘንድ መንገድ መከፈታችንን ተያይዞ ሀገር የሚያወድምና የተጀመረውን ለውጥ የሚያደናቅፍ ተግባር መፈፀም በመጀመራችን ለበርካታ ወገኖቻችን ሞት፣ መቁሰል ደሞም መፈናቀል ለበርካታ የሀገሪቷ ንብረት መውደም ምክኒያቶች እየሆንን ነው፡፡ ግራና ቀኙን ሳናይና ሳናስተውል በፌስ ቡክና በቲክ ቶክ(Tik Tok) ከጮኸው ጋር ሁሉ አብረን እየጮህን ማን ለምን ዓላማ እንደለቀቀው የማናውቀውን የብጥብጥ፣ የዘረኝነትን እና ሰላምን የማደፍረስ ጥሪ ተቀብለን በተባለው ሰዓትና ቦታ በመገኘት መሪ የሌለው ነውጥ በመፍጠር በብዙ ዓመታት የገነባናቸውን መሰረተ ልማቶች በአጭር ደቂቃዎች ውስጥ አፈር ድሜ ስናበላ ተስተውለናል፡፡

በርግጥ ዘመኗን ሙሉ አይደለም እንደ ሀገር እንደ ቤተሰብ እንኳን ሃሳብን በነፃነት ማንፀባረቅ ሀጢያት በነበረባት ሀገር ስር የሰደደን ሃሳብን የመግለፅ መብትን ከመቅፅበት ሙሉ በሙሉ ማጎናፀፍ ይቻላል ተብሎ ባይገመትም እንደ መንግስትም ይሁን እንደ ህዝብ ያሉትን አማራጮች ሁሉ በመጠቀም በሰላማዊ መንገድ ሃሳብን ለመግለጥ መሞከር አዋጭ የሆነ ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡ አሊያ ግን ትናንት ነፃነትን ሲናፍቋት የነበሩ የአረቡ ዓለም ሰዎች ባልተጠናና በማህበራዊ ድረ-ገፆች በሚለቀቁ መልዕክቶች በመገፋትና ስሜታዊ በመሆን በፈፀሙት ስህተት እስከ ዛሬ ሊወጡ የማይችሉበት ችግር ውስጥ ገብተው ይዳክራሉ፡፡

የቴክኖሎጂ ገፀ-በረከት የሆኑና በኢንተርኔት በኩል የምናገኛቸውን ማህበራዊ ድረ-ገፆችን የምንጠቀምባቸው መንገዶች ኃላፊነት የጎደለውና ተገኘ ተብሎ ግራ ቀኝ ሳይታይ የመጣልንን ሀሳብ ብቻ የምናሰፍርበት ከሆነ በርግጥም ለቴክኖሎጂው ያለን የዕውቀት ደረጃ የወረደ ነው ማለት ነው፡፡ ምክያቱም እያንዳንዱ የቴክኖሎጂ ውጤት ወደ ህዝብ ሲለቀቅ የራሱ የሆኑ የስነ-ምግባር መርሆዎች እንዳሉት እሙን ነው፡፡ በርግጥ እነዚህ የስነ-ምግባር መርሆዎች በአብዛኛው እኛው ተጠቃሚዎቹ ከልባችን መክረን የምንፈፅማቸው በመሆናቸው አስገዳጅነታቸው ብዙም የማይታይ ነው፡፡ ሆኖም ግን ተገኘ ተብሎ ሁሉ እንደማይበላ ሃሳብን ለመግለፅ ያለውን ሰፊና ከልካይ የሌለው መንገድን ብቻ በማየት ነገ ሀገራችንን ከማትወጣበት ማጥ ውስጥ እንድትገባ የሚያደርጉ ሃሳቦችን አሊያም ህዝቡ እንዲተገብራቸው የሚፈልጉ የጥቂት አካላትን ፍላጎት መለጠፉ በራስ ቤት ላይ ቤንዚን አርከፍክፎ እሳት የመጫር ያህል ነው፡፡ መቼም በዚህ ዘመናዊ ዘመን ላይ ሆነን ሃሳብን በተቃውሞ መግለፅ ‹‹ክልክል ነው!›› የሚል ማስታወቂያ ለጥፎ ከህዝቡ ጋር የሚፋጠጥ መንግስት ካለ የሚያራምደውን አስተሳሰብ ደግሞ ሊቃኝ ይገባል ባይ ነኝ፡፡ በተገላቢጦሹ ደግሞ ሕዝቡ ተቃውሞውንም ይሁን ሃሳቡን የሚገልፅበት መንገድ የተሳሳተ ከሆነ ቆም ብሎ እራሱን ሊመለከት የሚገባው እራሱ ሕዝቡ ነው፡፡

ሕዝብና መንግስት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ለመሆናቸው አጠያያቂ አይደለም እናም በሁለቱም ወገን መስማማት የሚባል ባህል ካልሰፈነ ነገን አንዳችን ከአንዳችን ላለመጠፋፋታችን ምን ዋስትና አለን?፡፡ ሃሳቦችን በፍትሀዊ መንገድ ማንሸራሸርና ዘገምተኝነትን አስወግዶ የመፍትሄ እርምጃዎችን አግባባዊ በሆነ መንገድ መመለስ እንደ መንግስት ሊያደርገው የሚገባና መገለጫው መሆኑን በማመን ለችግሮች አፋጣኝ መፍትሄዎችን በማስቀመጥ በሁለት አቅጣጫ እንደ ተሳለ ሰይፍ ልማቱን በአንድ ጎን እያፋጠነ በሌላ ጎኑ ደግሞ የሕዝቦቹ ትከሻ ላይ ተቀምጠው በመክበድ ፍላጎታቸውን ብቻ በማየት አይናቸው የታወሩ አላስተዋዮችን ከህዝቡ ፊት ዞር በማድረግ የብልህ ሥራ ሊሰራ ግድ ነው፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ተግባር እንደ መርህ... . . ! ! !

በዳግማዊ ፍቃዱ

ባሳለፍነው ሳምንት እትማችን እንግዳችን የነበሩት ባለታሪካችን አቶ ከተማ ዘለቀን ጨምሮ ቀድም ባሉት እትማችን በተከታታይ የጋዜጣችን እንግዳ ያደረግናቸው ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ሁሉም ለማለት በሚያስችል ሁኔታ ለስራቸው ስኬት የተለያዩ በዘርፉ ድጋፍ የሚሰጡ አካላት እገዛን መጠቀማቸው የውጤታማነት ጉዞአቸውን ካቀናላቸው ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ሲጠቅሱ ተመልክተናል፡፡ ከነዚህ ድጋፍ ሰጪ ባለድርሻ አካላት ውስጥ ድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም አንዱ ነው፡፡ ባለታሪኮቻችንም ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት ለመለወጣቸው ምክንያት መሆኑን ሲገልፁ ነበር፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ስራ ፈጣሪ ዜጎች ወደ ስራ ሲገቡ ሃሳብ እና እውቀት አለዚያም የመስሪያ ጉልበት ብቻ ሊኖራቸው ይችላል፤ሆኖም ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ በቂ የካፒታል መጠን አይኖራቸውም፡፡

ቀደም ሲል እንደገለፅነው በዚህ አምድ የምናቀርባቸው ባለታሪኮቻችንም ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት ለመለወጣቸው ምክንያት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ባሳለፍነው ሳምንት እትማችን እንግዳችን የነበሩት ባለታሪካችን አቶ ከተማ ዘለቀ ከተቋሙ ያገኙትን አገልግሎት የገለፁትን በምሳሌነት እንጥቀስ፡፡

´´ ከአስራ ሰባት አመት በፊት የግል ስራ ለመጀመር ሳስብ በእጄ ላይ መነሻ የሚሆን ካፒታል የለኝም ነበር፡፡ይሁን እንጂ ያለኝን አማራጭ ማሰብ ጀመርኩ እናም የመኖሪያ ቤቴ ያረፈበት አነስተኛ መሬት በዋስትና በማሲያዝ ብር ተበድሬ ስራ ለመጀመር አሰብኩ፡፡

ወደ ድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም በማምራት ሃሳቤን አማከርኳቸው፡፡ እርግጥ ከአስራ ሰባት አመት በፊት አነስተኛ ሆቴል ለመክፈት ሳስብ ስፍራው እንደዛሬው የሞቀ የንግድም ሆነ የመኖሪያ ስፍራ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ ድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ሃሳቤን በመቀበል ከጎኔ ለመቆም ፍቃደኛ ሆኑ፡፡እናም ዛሬ ላይ ለደረስኩበት ለውጥ መነሻ መሰረቴ በመሆናቸው በቃላት ገልጬ የማልጨርሰውን ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለው፡፡´´ሲሉ ነበር ምስክርነታቸውን የሰጡን፡፡

በግልም ሆነ በተቋም ደረጃ መልካም ነገር የሚሰራ ሁሉ ሊበረታታና ሊመሰገን እንደሚገባው ሁሉ በዛሬው እትማችን የዚህን ተቋም የስራ እንቅስቃሴ ለመቃኘት አቶ ተሾመ አበበ አዱኛ የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ዋና ስራ አስፈፃሚ እንግዳችን አድርገን ቀርበናል፡፡መልካም ንባብ፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡-አቶ ተሾመ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

አቶ ተሾመ አበበ ፡-እኔም ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡-መልካም አቶ ተሾመ ....!! ቆይታችንን ከትውውቅ እንጀምርና የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ታሪክን እናውሳ፡፡መቀጠል ይቻላል....፡፡

አቶ ተሾመ አበበ ፡-የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ጉዞ ሁለት አስርት አመታትን ተሻግሯል ፡፡ ተቋሙ በ1994 ተመስርቶ ከምስረታው ሁለት አመታት በኋላ በ1996 ዓም ስራ የጀመረ ሲሆን ለበርካታ አመታት በድሬደዋ ብቻ አገልግሎት እየሰጠ ቆይቷል፡፡ ከቅርብ አመታት ወዲህ ደግሞ በአጎራባች ክልሎች አገልግሎቱን ማስፋት ችሏል፡፡






ተቋሙ በተለይም መስራት ለሚችሉ ሆኖም በአቅም ችግር በድህነት ለመኖር ለተገደዱ ዜጎች ፤ ለስራ አጥ ወጣቶች የብድርና ቁጠባ አገልግሎት በማቅረብ ለዜጎች ህይወት መለወጥ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ልማት አጋርነቱን እያስመሰከረ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

አገልግሎቱን የበለጠ በማዘመን ብሎም ተደራሽነቱን በማስፋት የደንበኞቹን እርካታ ለመጨመር በየጊዜው የሚሰጠውን የብድር መጠን ፤ የዋስትና ግምቶች ፤ወለድና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ላይ ማሻሻያ በማድረግ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ! ! ! ፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ ለተሰማሩና መሰማራት ለሚፈልጉ በዝቅተኛና መካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶችና ወጣቶች የደንበኛና ፍላጎት ያማከለ የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶች በመስጠት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ማስቻልን ተልእኮ አንግቦ እየሰራ የሚገኘው ይህ ተቋም ለበርካቶች ህይወት መለወጥ ቁልፍ አቅም መሆን የቻለና እየሆነ የሚገኝ ለመሆኑ በርካታ ማነፃጸሪያዎችን እየጠቀሱ ማሳየት ይቻላል፡፡ የተቋሙ ደንበኞችም ለዚህ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡

ምንም እንኳን በርካታ አመታትን አገልግሎቱን ለደንበኞቹ እያቀረበ ያለ ተቋም ቢሆንም ከውጤታማነት አንፃር ሲለካ ያን ያክል አመርቂ ደረጃ ላይ መድረስ አልቻለም ነበር፡፡ በመሆኑም በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በተደረጉ ማሻሻያዎች በየዘርፉ ወሳኝ የለውጥ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡-የተቋሙ እድገት ከአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ እንዴት ይገለፃል?

አቶ ተሾመ አበበ ፡- ከአገልግሎት አሰጣጥ አኳያ ሲመዘን ተቋሙ በ1996 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት ሲጀምር በአንድ የብድር አይነት ማለትም በቡድን ብድር ብቻ ነበር፡፡ በሂደትም ከአቻ ተቋማት ልምዶችንና ተሞክሮዎችን በመውሰድ ፣ የሪፎርም ሥራዎችን ተግባራዊ በማድረግ አዳዲስ የብድር እና የቁጠባ አማራጮችን በመቅረፅ አገልግሎቱን ለማስፋት ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት በመደበኛው ፣ በወለድ አልባው እና በማሽነሪ ሊዝ የሚከተሉትን የብድር እና የቁጠባ አማራጮችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

በመደበኛው የብድር አገልግሎት የቡድን ብድር ፤ የግል ብድር ፤ የማህበር ብድር ፤ የቤት መስሪያ ብድር ፤ የፍጆታ ብድር ፤ የተሽከርካሪ ብድር ለደንበኞች ያቀርባል፡፡ በዚህ አገልግሎት ተጠቅመው ውጤታማ የሆኑት በርካቶች ናቸው፡፡

የካፒታል ዕቃ ኪራይ (Machinery Lease) አሁን ላይ በርካታ ዜጎችን ከፍ ባለደረጃ ተጠቃሚ እያደረገ የሚገኝ ተቋሙ በተጠና መልኩ እየሰጠ ከሚገኘው አገልግሎቶች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

በመደበኛው የቁጠባ አገልግሎት !!! የደብተር ቁጠባ ፤ የተበዳሪዎች የውዴታ ግዴታ ቁጠባ ፤ የታዳጊዎች ቁጠባ ፤ የጣምራ ቁጠባ ፤ የጊዜ ገደብ ቁጠባ ፤የቤት ለቤት ቁጠባ ፤ የሳጥን ቁጠባ አገልግሎትን ተቋሙ ይሰጣል፡፡ ይህንን አገልግሎት ተጠቅመው በስራቸው ላይ ለውጥ ማምጣት የቻሉ ደንበኞች በርካታ ናቸው፡፡

በወለድ አልባ ብድር ሁለት አገልግሎቶችን ለደንበኞች ይሰጣል፡-

የመጀመሪያው ሙራባሀ የሚባለው ሲሆን በሸሪዓ ለተፈቀደ የሥራ መስክ ደንበኛው የሚፈልገውን ዕቃ / ንብረት/ በዓይነት በመግዛት የተወሠነ የትርፍ ጭማሪ ታክሎበት የሚሰጥ ብድር ነው፡፡

ሁለተኛው ኢጃራ በመባል የሚጠራው ለሥራ የሚያገለግሉ ማሽኖችን ወይም ተሽከርካሪዎችን ገዝቶ ማከራየት ፣ ተከራይ በውሉ መሠረት ክፍያውን ከፍሎ ሲጨርስ ንብረቱ የራሱ የሚሆንበት ብድር ነው፡፡

እንደ ወለድ አልባ ብድር አቅርቦት ሁሉ ከወለድ አልባ የቁጠባ አገልግሎት በድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ይሰጣልዋዲአ (የተቀማጭ ቁጠባ) እና ሙዳረባ (የኢንቨስትመንት ቁጠባ) በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ድሬ ጋዜጣ ፡-ከተደራሽነት አኳያ የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም እንዴት ይመዘናል ?

አቶ ተሾመ አበበ ፡- በችግር ጊዜ ለተጠጉት ደራሽ የሆነው የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም ከተደራሽነት አንፃር ባከናወናቸው እና እያከናወናቸው የሚገኙ ስራዎች ከተጠቃሚው ዘንድ በስፋት መድረስ እየቻለ ሲሆን አሁን ላይ ከብሄራዊ ባንክ ባገኘው ፈቃድ መሠረት በድሬዳዋ ከተማ አንድ ማዕከላዊ ዋና ቢሮ ፣ 7 ቅርንጫፎችን እና 3 ንዑስ ቅርንጫፎችን እንዲሁም በገጠር በ4ቱ ክላስተሮች ንዑስ ቅርጫፎች በሚሰጠው አገልግሎት ሳይወሰን በሐረር ከተማ 2 ቅርንጫፎችን እና በጅግጅጋ ከተማ ደግሞ 1 ቅርንጫፍ ከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ደግሞ በአዲስ አበባ ቅርንጫፎችን ለመክፈት የአዋጭነት ጥናቱን አጠናቆ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

ለሁለት አስርት አመታት የብድና ቁጠባ አገልግሎትን እንደየዘመኑ እየተሻሻለ ለደንበኞች አገልግሎቱን በመስጠት የዘለቀው የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም በቀጣይ ወደ ከፍተኛ የፋይናንስ ተቋም የመሸጋገር ትልምን አንግቦ እየሰራ ሲሆን ወደዚህ ደረጃ የሚያበቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ከወዲሁ መልክ መልክ እያሲያዘ በመጓዝ ላይ ነው፡፡

ከመነሻው አንግቦ ከተነሳው የደንበኛን ፍላጎት ያማከለ የብድርና ቁጠባ አገልግሎቶች በመስጠት ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ከማስቻል በተጨማሪ በቀጣይ በፋይናንስ አቅርቦቱ ዘርፍ በአገር አቀፍ ደረጃ አማራጭና ተወዳዳሪ ተቋም ለመሆን ሩቅ በማለም የቅርቡን እውን እያደረገ ወደ ፊት የሚጓዝ ነው ...... የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም !! ለዜጎች ህይወት መለወጥ ብሎም ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ልማት አጋርነቱን እያስመሰከረ እስከ ስኬቱ ጫፍ ከደንበኞቹ ጋር ይዘልቃል፡፡

የተከበራቹ አንባቢያን በአስተዳደራችን ስራ ፈጣሪ ወጣቶች ለስራቸው ስኬት የተለያዩ በዘርፉ ድጋፍ የሚሰጡ አካላት እገዛን ከሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት አንዱ የሆነውን የድሬ ብድርና ቁጠባ ተቋም የዳሰስንበትን ጥንቅር እዚህ ላይ አበቃን፡፡ እስከሳምንት ቸር ቆዩን፡፡ሰላም....!

# ያልተገራው . . .

ከገጽ 4 የዞረ

በተጨማሪም የሚዲያ ሰዎቻችን የበላይ አካላት የሚሏቸውን ብቻ ከማንፀባረቅ ከህዝቡ ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የልቡን እንዲናገር ነፃ መድረኮችን ማመቻቸትና በመናገራቸው የሚደርስባቸውን ማዋከብ መከላከያ መንገዶችንም በማመቻቸት የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር የሚጠይቀውን ተግባር አሁን እያከናወኑ ካሉት በላይ ቢያከናውኑ በየ ማህበራዊ ድረ-ገፆች በዘፈቀደ የሚለቀቁ ያልተጠኑና በዘፈቀደ የህዝቡን ልብ የሚሸረሽሩ ደግሞም በተሳሳተ መንገድ እንዲሄድ የሚያደርጉ ዘረኝነትንና ‹‹የኔ ሀሳብ ብቻ ትልቅ›› ነው የሚሉ መልዕክቶችን መቀነስ እንደሚቻል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

ዛሬ በፌስቡክና በቲክ ቶክ(Tik Tok) ድረ-ገፆች ላይ ‹‹ሆ›› ካለው ጋር ምኑም ሳይገባን ‹‹ሆ›› ብለን አንድም ለብዙዎች መፈናቀል ደግሞም ለነገ ሀገር ተረካቢ ታዳጊዎች ፅንፍ የወጣ ዘረኝነትን ለማውረስ መሯሯጥ የውጤቱን ቅንጫቢ ከወዲሁ እያየን ነው፡፡ በዚሁ ሁኔታችን ከቀጠልን ደግሞ የዘራነውን ዘር ሙሉ በሙሉ የጥላቻን ፍሬ አሽቶ ለአጨዳ እንደሚደርስ እሙን ነው፡፡ ወዳጆቼ እንዲህ ብዬ ባበቃስ ዘረኝነትንና ጥላቻን ከሚያንፀባርቁ የፌስቡክና የቲክ ቶክ(Tik Tok) ጫጫታዎችና ሆታዎች እራሳችን አልሰማም፣ አላይም ደሞም አልናገርም በማለት ‹‹ሆ›› ካለው ጋር ‹‹ሆ›› ባለማለት እራሳችንም ድነን ትውልዱንም ከጥላቻ አስተሳሰብ የምናድን ያድርገን ብልስ ‹‹አሜን›› ትሉ ይሆን? እንግዲህ አባቶቻችን እንደሚሉት ‹‹አሜን›› ላላችሁ አሜን ይሁንላችሁ፡፡ አበቃሁ ቸር ሁኑልኝ፡፡

# በኤች አይ ቪ/ኤድስ ላይ የሚታየው ቸልተኝነት ይቁም !

በበድሉ ሀይሌ

ወጣቶችን ጨምሮ ለበሽታው ተጋላጭ ተብለው በተለዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የኤች አይ ቪ/ኤድስ የሥርጭት ምጣኔ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ እየተነገረ ይገኛል፡፡ እኛም ይህ ፅሁፍ ስናዘጋጅ አብዛኛው መረጃውችን የወሰድነው በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ36ኛ እንዲሁም በኢትዮጵያ ለ35ኛ ጊዜ «የማኅበረሰብ መሪነት ለላቀ ኤች አይ ቪ መከላከል» በሚል መሪ ቃል ኅዳር 2016 ዓ.ም. የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቀን ሲከበር በቀረበው ሰነድ ላይ ተመስርተን ለጋዜጣ ፅሁፍ እንዲመች አድርገን አቅርበነዋል፡፡

በዘንድሮው የአለም ኤድስ ቀን “የማህበረሰብ መሪነት ለላቀ ኤች አይ ቪ መከላከል” በሚል መሪ ቃል ህዳር 2016 ዓ.ም ታስቦ መዋሉ ይታወቃል፡፡ ማህበረሰቡ ኤች.አይ.ቪን በመከላከል ረገድ የሚጫወተው የማይተካ ሚና በአገር አቀፍ ደረጃና እስከታች ባለው የመንግስት መዋቅርና በማህበረሰብ አደረጃጀት ዕውቅና የሚሰጥበት ብቻ ሳይሆን በቀጣይ ማህበረሰቡን በማብቃት ወደ መሪነት ደረጃ ለማምጣት እንዲሁም የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ምቹ ሁኔታዎች የተፈጠሩበት ጊዜ እንደነበሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ማህበረሰቡ በኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም ዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ፣ ክትትል እና ግምገማ እንዲሁም ሃብት ማሰባሰብና አስተዳደር ላይ የመሪነት ሚናውን እንዲወጣ ማስቻል ትልቁ ጥረት ነው፡፡ በቂ እና ቀጣይነት ያለው የህብት ድጋፍ በማድረግ ማህበረሰቡ በኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም ላይ ያለው የመሪነት ሚና እንዲወጣ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ማህበረሰቡ በኤች አይ ቪ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራም የመሪነት ሚናውን እንዳይወጣ የሚያደርጉ መሰናክሎችን በማስወገድ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች ላይ በስራ ቦታ እና በማህበራዊ ህይወት የሚደርሰዉን የአድሎና መገለልን ማስቀረት ይገባል፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት 0.9% ቢሆንም፤ የቫይረሱ ስርጭት ከቦታ ቦታ እንዲሁም ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል፡፡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በጾታ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ልዩነትና በተሰማሩበት የሥራ ባህሪያቸው ምክንያት የኤች.አይ.ቪ. ተጋላጭነታቸው ይለያያል፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የስርጭቱ ሁኔታ በጾታ ሲታይ 60 % የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት በሴቶች ላይ ይታያል፡ ፡ በከተማ ያለዉ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት ከገጠር አንፃር ሲታይ በከተማ ያለዉ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት በሰባት እጥፍ ከፍ ያለ ነዉ፡፡ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች (PLHIV population) 610,350 (M- 238,853 : F- 371,497) የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት (Adult HIV prevalence) 0.9% አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የሚያዙ ሰዎች (New HIV infections) 8,257 ( M - 3,185 F - 5,072 በኤድስ ምክንያት የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር (Annual AIDS deaths) - 11,322 ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች (PLHIV population) 11,096 (M- 4,388 : F- 6,708 ) የኤች.አይ.ቪ. ስርጭት (Adult HIV prevalence) 2.9% መሆኑን በቅርብ የተጠናው ጥናት ያሳያል፡፡

አዲስ በኤች.አይ.ቪ. የሚያዙ ሰዎች (New HIV infections) 244 (M= 100 F=144) በኤድስ ምክንያት የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር (Annual AIDS deaths) 307 በ2030 ኤድስን የማቆም ራዕይ ከግብ ለማድረስ አገሮች ስምምነት ተቀብለው መተግበር ላይ ይገኛሉ፡ ፡ ሀገራችንም ይህንን ራዕይ ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ግቦችን አስቀምጣ በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ የተቀመጡ ግቦችም እ.አ.አ በ2025 ሶስት ዘጠና አምስቶችን ማሳካት ሲሆን፤ ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የሚገኙ ሰዎች ውስጥ 95% የሚሆኑትን ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፣ ተመርምረው ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው የተገኘባቸዉን ሰዎች 95% የሚሆኑትን የጸረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ እና ህክምና ከጀመሩት ሰዎች ውስጥ ደግሞ 95% የሚሆኑትን ህክምናቸውን በትክክል ተከታትለው በደማቸው ውስጥ ያለውን የቫይረስ ልኬት መጠን በዝቅተኛ ደረጃ (50 cc/ml) እንዲሆን በማድረግ እንደሆነ ተነግሯል፡፡

የተመዘገቡ ዉጤቶች የኤች አይ ቪ በደማቸው







ይገኛል ተብሎ ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 84 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁና ከእነዚህ መካከል 98 በመቶ ያህሉን ደግሞ የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሀኒት እንዲጠቀሙና መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 96.3 በመቶ ያህሉን የቫይረስ ልኬት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዲወርድ ማድረግ ተችሏል (2022 HIV spectrium)፡፡

በዓመት ውስጥ የሚኖረውን በኤድስ ምክንያት የሚከሰትን ሞት መጠን በ2010 ከነበረበት 125/100,000 በ2022 ወደ 11/100,000 በማውረድ ከ52 ከመቶ በላይ መቀነስ ተችሏል (2022 HIV spectrium)፡፡ ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2010 ከነበረበት 46% እ.ኤ.አ በ2022 ወደ 12% በመቶ እንዲቀንስ ተደርጓል (2022 HIV spectrium)፡፡

ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ጥምረት ማህበራት በኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ፕሮግራሞች ዕቅድ፣ ትግበራ፣ ክትትልና ግምገማ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ እንዲያረጉና የበኩላቸውን አስተዋፆ እንዲያበረክቱ መደረጉ፣ ኤች አይ ቪ በደማቸው ከሚገኝ እናቶች የሚወለዱ ህፃናት በወቅቱ የምርመራና ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የማፋጠኛ (accelerated plan) ዕቅድ በማዘጋጀት የተሰሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸው ታውቋል፡፡

ዋና ዋና ተግዳሮቶች ከዚህ ቀደም በየደረጃዉ የነበረው የአመራሩ ቁርጠኝነት ዛሬ ላይ መታየት አለመቻል (ለምሳሌ፡- ተቋማት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ሜይንስትሪሚንግ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር)፡፡ በኤች አይ ቪ መከላከል በጥልቅ የባህሪ ለውጥ ተግባቦት ስራዎች የተደረሱ በተለይም ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች የሚሰሩ ሰራተኞች እና ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሆኑ አፍላ እና ወጣት ሴቶች የኤች አይ ቪ ምርመራ አገልግሎት ተጠቃሚ ከማድረግ አንፃር የጎላ ክፍተት መኖሩ ተመላክቷል፡፡

የኤች አይ ቪ ምርመራ አገልግሎት በመንግስትና እና የግል የጤና ተቋማት እንዲሁም ማህበረሰቡ ድረስ በመዝለቅ የተለያዩ የምርመራ ስልቶችን በመተግበር እየተሰጠ የሚገኝ ቢሆንም ቫይረሱ በደማቸው ያለ ሰዎችን ከማግኘት አንፃር የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ መሆን አለመቻሉ፤ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ከሚገኝ እናቶች የተወለዱ ህፃናትን በጊዜው የኤች አይ ቪ ምርመራ እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ክፍተት መኖሩ፤ ኤች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የተያዘውን ግብ ለማሳካት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተከታታይነት ያላቸዉ ፕሮግራሞች ቢተገበሩም ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት የኤች አይ ቪ መከላከያ መድሃኒት (NVP +AZT Prophylaxis) ዝቅተኛ አፈፃፀም ይኖረዋል፡፡

ዋና ዋና ተግዳሮቶች የኤች አይ ቪ ፕሮግራም ግብአቶች መቆራረጥ (ለአብነትም የኮንዶም አቅርቦት፤ የኤች አይ ቪ መመርመሪያ ኪቶች፤ የአባላዘር በሽታዎች ህክምና ኪት) ለኤች አይ ቪ መከላከል እና መቆጣጣር በተለይም ማህበረሰቡ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች ራሳቸውን ይፋ አድርጎ በማስተማር፤ የማይተካ ሚና በመጫወት የበኩላቸውን አስተዋፆ ሲያበረክቱ የቆዩ ቢሆንም ከበቂ ድጋፍ እጦት የተነሳ ቫይረሱ በደማቸው የሚገኝባቸው ማህበራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ እና እየፈረሱ መምጣት ይጠቀሳል፡፡

የሚዲያ ተቋማት የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ሥራዎችን የራሳቸው አጀንዳ አድርገው ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ ከመፍጠርና ማህበራዊ ኃላፊነት ከመወጣት አንፃር ክፍተት መኖሩ፣ በመጀመሪያው 95% እንደ ሀገር የኤች አይ ቪ በደማቸው ይገኛል ተብሎ ከሚገመቱ ወገኖች መካከል 84 በመቶ የሚሆኑት ተመርምረው ራሳቸውን ያወቁ ሲሆን አሁንም የመጀመሪያ 95% ከማሳካት አንፃር ክፍተት አለ፡፡

በማህበረሰብ ደረጃ መረጃዎችን ለያይተን ስንመለከት ለኤች.አይ.ቪ. በይበልጥ ተጋላጭ ሆኖ የሚታዩት የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሚከተለዉ ከዚህ በታች በዝርዝር ተመላክቷል

የሴተኛ አዳሪዎች (23 %) አደንዛዥ እፅ በመርፌ የሚወስዱ ሰዎች (14 %) የህግ ታራሚዎች (4.2 %)፤ የትዳር አጋራቸዉ የሞተባቸዉ (11.5 %)፤ ከትዳር አጋራቸዉ ጋር የተለያዩ/የተፋቱ (2.9 %)፤ የረጅም ርቀት መኪና አሽከርካሪዎች (4.9 %)፤ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የሚሰሩ ሰራተኞች የአፍላ ወጣቶች (Adolescents) ሴቶች እና ወጣቶች (Youths) ሴቶች (እድሜያቸዉ ከ15-24) መለዮ ለባሾች (High-risk uniformed ) (1.2 %) ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች የትዳር አጋር በሃገራችን ለኤች.አይ.ቪ. ስርጭት መንስዔ ናቸዉ ተብለዉ ከተለይቱ ምክንያቶች ዉስጥ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋናዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡

በማህበረሰቡ ዉስጥ ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መተላለፊያ መንገድ ያለዉ ግንዛቤ አናሳ መሆን በሃገራችን አጠቃላይ ስለ ኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያዉ እና መከላከያ መንገድ በማወቅ ደረጃ በወንዶች 39 % ፤ ሲሆን በሴቶች 20 % ነዉ፡፡ (EDHS 2016) በድሬዳዋ አጠቃላይ ስለ ኤች.አይ.ቪ. መተላለፊያዉ እና መከላከያ መንገድ በማወቅ ደረጃ በወንዶች 64 % ፤ ሲሆን በሴቶች 45 % ነዉ፡፡ (EDHS 2016)

የሴተኛ አዳሪነት እና ወሲብን በጥቅም የመለወጥ ሁኔታዎች በብዛት መስፋፋት በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ሴተኛ አዳሪ የሚገቡ ታዳጊ ወጣቶች ቁጥር እየጨመረ ነዉ፡፡ የኤች.አይ.ቪ. አገልግሎቶችን የመጠቀም ባህል አናሳ (Low health seeking behavior) መሆን፣ ከአንድ በላይ የወሲብ አጋር በተመሳሳይ ወቅት መያዝ ፤ኮንዶም የመጠቀም ሁኔታ አነስተኛ መሆንና 49 % የሚሆኑ ወንዶች በጊዜያዊ ከተዋወቋት ሴት ጋር ያደረጉትን ግንኙነት ኮንዶም አልተጠቀሙም፡፡

ወጣቶች በትንሽ እድሜ ወሲባዊ ግንኙነት መጀመር እድሜያቸዉ ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች (በተለይ ሴቶች) የግብረ ስጋ ግንኙነት በእድሜ ከሚበልጣቸዉ ሰዎች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ በጣም እየጨመረ ነዉ፡፡ ጥንቃቄ የጎደለዉ የወሲብ ግንኙነት የሚያደርጉ ወጣቶች ቁጥር መብዛት በዚህም ምክንያት ድንገተኛ የእርግዝና መከላከያ (post pill) ተጠቃሚዎች ቁጥር መብዛት፤ ውርጃ ሚፈፅሙ ወጣቶች ቁጥር መብዛት፤ እና ያልተፈለገ እርግዝና የሚከሰትባቸዉ ታዳጊ ወጣቶች (teen age pregnancy) ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመር እየተስተዋለ ነዉ፡፡

የአባላዘር በሽታ ስርጭት መስፋፋት አልኮል እና አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ መብዛት ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉ ሰዎች ህክምናቸዉን በአግባቡ አለመከታተል የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና በመከታተል ላይ ያሉ ሰዎች በተለያዩ ምክንያት ህክምና እያቋረጡ ነዉ፡፡ የአድሎ እና መገለል ኤች.አይ.ቪ. በደማቸዉ ያለባቸዉን ሰዎች ማግለልና መድሎ መፈፀም ቫይረሱን ለመቆጣጠር ለሚደረገዉ ጥረት ትልቅ እንቅፋት እየሆነ ነዉ፡፡

በሃገራችን ላለፉት አመታት ኤች.አይ.ቪን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ሁሉን አቀፍ የኤች.አይ.ቪ. መከላከል (HIV combination prevention) እስትራቴጂን በመከተል ላይ እንደሆነች ይታወቃል፡፡ ሁሉን አቀፍ የኤች.አይ.ቪ. መከላከል አገልግሎቶችን በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ይጠቃለላሉ፡፡

I.የኤች.አይ.ቪ. መከላከል (HIV Prevention Programs)

- ትምህርታዊ ፕሮግራሞች
- የባሃሪ ለዉጥ ፕሮግራሞች (የአቻ ለአቻ፤ የህይወት ክህሎት፤ ወዘተ)
- የኮንዶም አቅርቦትና ስርጭት
- የአልኮል እና ሌሎች ዕፆችን ተጽዕኖአቸውን መቀነስ እና ማስወገድ (Risk reduction)

II.የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የሕክምና አገልግሎቶች (Bio-medical services)

- የኤች.አይ.ቪ. ምክርና ምርመራ አገልግሎት
- የፀረ-ኤች አይ ቪ መድኃኒቶች ሕክምና አገልግሎት
- ኤች.አይ.ቪ. ከእናት ወደ ልጅ/ጽንስ እንዳይተላለፍ ህክምና አገልግሎት
- ከኤች.አይ.ቪ. ጋር ተዛማጅነት ያላቸው በሽታዎች ሕክምና (የቲቢ፤ የአባላዘርና ቫይራል ሄፓታይተስ በሽታዎች ህክምና)

III. መዋቅራዊ ፕሮግራሞች (Structural intervention) ፡-

- ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከል አዎንታዊ አስተዋፆ ሊያበረክቱ የሚችሉ አሰራሮችና ህጎችን ተግባራዊ ማድረግ እንዲሁም አሉታዊ አስተዋፆ ያላቸዉን ማስተካኪያ እንዲደረግባቸዉ ማድረግ፡፡

የኤች.አይ.ቪ. የምክክርና ምርመራ አገልግሎት (HCT) ዓይነቶች

- በፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ. ምክር እና ምርመራ አገልግሎት /VCT/
- በጤና ባለሙያ አነሳሽነት የሚከናወን የኤች.አይ.ቪ. ምርመራና ምክር አገልግሎት (PITC)
- ኤች.አይ.ቪ. እራስን በራስ መመርመር (HIV self-test)

የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ሕክምና አገልግሎት አንድ ሰው ተመርምሮ ኤች.አይ.ቪ. በደሙ ውስጥ ከተገኘ በጤና ባለሙያ ትዕዛዝ መሠረት ወዲያውኑ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት ይጀምራል፡፡ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት በጤና ባለሙያ በታዘዘዉ መሰረት በአግባቡ የሚወሰድ ከሆን የሚከተሉት ጥቅሞችን ያገኛል፡-

- የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ መጠን እንዲቀንስ (ኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በሰዉነት ዉስጥ እንዳይባዛ ይረዳል)
- የሰውነታችን የበሽታ መከላከያ ሲዲ4 መጠን እንዲጨምር ይረዳል
- የተጓዳኝ በሽታዎችን እና ሞትን ለመከላከልና ለመቀነስ ያግዛል
- ጤናማ ሕይወት ለመኖር ያግዛል
- ኤች.አይ.ቪ. ወደ ሌላ ሰዉ መተላለፍን ይገታል እንዲሁም ለቫይረሱ ስርጭት መቀነስ ትልቅ አስተዋፆ ያበረክታል፤

የአድሎና መገለልን ፍራቻ ብዙ ሰዎች የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና አይከታተሉም፡፡ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. መድሃኒት በአግባቡና ሁልጊዜ ከተወሰደ በሰውነት ውስጥ ያለ የቫይረስ መጠን ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይፋ በተደረገው ሳይንሳዊ ግኝት መሠረት የፀረ-ኤች.አይ.ቪ. ህክምና የሚከታተል ታካሚ ጥሩ የመድሃኒት አወሳሰድ ካለዉ፡፡ በደሙ ያለዉ የቫይረስ መጠን ወደ ማይታይበት ደረጃ ይደርሳል፡፡

በዚህም በአንድ ሚሊ ሊትር ደም ውስጥ ያለው የቫይረስ መጠን ከ50 ኮፒ በታች ይወርዳል፡፡ በሰውነት ውስጥ ያለ የቫይረስ መጠን በላቦራቶሪ ምርመራ ወደ ማይታይበት ደረጃ ዝቅ (የማይታይ መጠን ሲደርስ) ጥቅሞቸ ያስገኛል፡፡ ታካሚዉ ለተጓዳኝ በሽታ ያለውን ተጋላጭነት በከፍተኛ ደረጃ ይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ ታካሚዉ ጤናማ እና የዕለት ተዕለት ሥራውን እና

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ዘመኑ የዲጂታል ነው

በኤደን ሳሙኤል

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ የድሬ ጋዜጣ አንባቢያን እንዴት ከርማቹሀል ሳምንታችሁ በመልካም እንዳለፈ ተስፋ እያደረኩ ለዛሬ ወዳዘጋጀሁላችሁ ፅሁፍ ቀጥታ ሳመራ፣ በስፋት የማወራችሁ ስለ ዲጂታል ባንኪንግ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ያለንበት ዘመን በኢትዮጵያ በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች እየቀነሱ በዛው ልክ ደግሞ ምስጋና ለቴክኖሎጂ ይግባና ዘመናዊ/ ዲጂታል/ የገንዘብ ዝውውሮች የበረከቱበት ነው፡፡

ይሄ ደግሞ ጊዜን ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ከእንግልት ነፃ መሆኑም ሀቅ ነው፡፡ በዚህም ለዛሬ ስለ ዲጂታል ባንኪንግ እንዲሁም ሀገራችን በዚህ ቴክኖሎጂ ምን ያህል እየተጠቀመች እንደሆነ እንቃኛለከን፡፡ ውድ አንባቢያን ለዚህ ፅሁፍ የተለያዩ የቢዝነስና የኢኮኖሚክስ ድህረ ገፆችን እንዲሁም የዩቲዩብ ቻናሎችን በዋቢነት እንደተጠቀምኩ ልብ ይባልልኝ፡፡

በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ባንኮች የሚደረጉ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የዲጂታል አማራጮች እየተተገበሩ ነው፡፡ በተለይ በ2015 ሒሳብ ዓመት እንደ ሪከርድ የሚቆጠር አፈጻጸም መታየቱም ይገልጻል፡፡ በ2016 ሒሳብ ዓመትም ቢሆን በዲጂታል ባንክ አገልግሎት የሚንቀሳቀሱ የገንዘብ መጠን እያደገ ስለመምጣቱ እየወጡ ያሉ መረጃዎች እያመላከቱ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋዊ መረጃ እንደሚያሳየውም፣ በተጠናቀቀው የ2015 ሒሳብ ዓመት በዲጂታል የክፍያ አማራጮች የተንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን ከ4.7 ትሪሊዮን ብር በላይ ደርሷል፡፡ ይህ የገንዘብ መጠን ከቀዳሚው ዓመት የ2014 የሒሳብ ዓመት ጋር ሲነፃፀር፣ ከ3.1 ትሪሊዮን ብር በላይ ብልጫ አለው፡፡ በግብይት መጠንም ቢሆን በ2014 የሒሳብ ዓመት የተፈጸመው ትራንዛክሽን ወይም ግብይት 345.7 ሚሊዮን ሲሆን፣ በ2015 ሒሳብ ዓመት ግን 1.24 ቢሊዮን ደርሷል፡፡

በተለይ በሞባይል ባንክ አገልግሎት እየተደረገ ያለው የገንዘብ ዝውውር ከሌሎች አማራጮች በተለየ ከፍተኛ አፈጻጸም የታየበት ሆኗል፡፡ የብሔራዊ ባንክ መረጃም የ2015 የሒሳብ ዓመት ብቻ ከ479.9 ሚሊዮን በላይ ትራንዛክሽኖች ከ3.44 ትሪሊዮን ብር በላይ በሞባይል የባንክ አገልግሎት ማንቀሳቀስ መቻሉን ነው፡፡

በሞባይል የባንክ አገልግሎት በሒሳብ ዓመቱ የተደረገው የገንዘብ ዝውውር ከሌሎች የዲጂታል አማራጮች አንፃር ሲታይ ከ80 በመቶ የሚሆነውን ሊይዝ ችሏል፡፡ ይህም ከሞባይል ባንክ አገልግሎት ጋር ተያይዘው ካሉ የቀደሙት ዓመታት እንቅስቃሴዎች አንፃር፣ ሲታይ በእርግጥም በኢትዮጵያ በጥሬ ገንዘብ ይደረግ የነበረ እንቅስቃሴን የለወጠ ስለመሆኑ ያሳያል፡፡ በሒሳብ ዓመቱ ያሳየው ዕድገትም በተገልጋዮች ዘንድ አገልግሎቱ እየተለመደ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱን ነው፡፡

በ2015 በሞባይል ባንክ የተደረገው ትራንዛክሽን ከ2014 ሐሳብ ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከ390 ሚሊዮን በላይ ብልጫ አለው፡፡ የተንቀሳቀሰውም የገንዘብ መጠን ከ2014 ጋር ሲነፃፀር ከ2.2 ትሪሊዮን ብር በላይ ብልጫ ማሳየቱ፣ ከዲጂታል የክፍያ አማራጮች የሞባይል ባንክ አገልግሎት ሰፊ በሆነ ልዩነት እያደገ መምጣቱን ነው፡፡

ከሞባይል ባንክ አገልግሎት ሌላ በኢንተርኔት የባንክ አገልግሎት የተንቀሳቀሰውም የገንዘብ መጠን በ2015 ከፍተኛ ዕድገት መሆኑን የሚጠቁመው መረጃ፣ በኢንተርኔት የተንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን 380.3 ቢሊዮን ብር ደርሷል፡፡ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ከፍተኛ የሚባለውን ገንዘብ እያንቀሳቀሰ የሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት በዓመት ከሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ ውስጥ አብዛኛው በዲጂታል አማራጮች የተፈጸሙ መሆኑን በጥሬ ገንዘብ የሚደረገው እንቅስቃሴ እየቀነሰ ለመምጣቱ አመላካች ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ በ2014 የሐሳብ ዓመት ከ64 በመቶ በላይ የሚሆነው የገንዘብ እንቅስቃሴው በዲጂታል የባንክ አገልግሎት የተሳለጠ መሆኑንና አሁንም በዚህ አገልግሎት የሚደረገው እንቅስቃሴ እየጨመረ መሄዱን አመላክቷል፡፡ ሰሞኑንም የ2016 የሐሳብ ዓመት




የዲጂታል የባንክ አገልግሎቱን በተመለከተ ይፋ ያደረገው መረጃ፣ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ዕድገት ቀጣይነት ያሳየ ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃ መሠረት በ2016 የሐሳብ ዓመት ግማሽ ዓመት ብቻ ከ2.8 ትሪሊዮን ብር በላይ በዲጂታል የባንክ አገልግሎት ገንዘብ ማንቀሳቀስ ችሏል፡፡ ይህ ገንዘብ እንቅስቃሴ ከ494 ሚሊዮን ብር በላይ በሚሆኑ ግብይቶች ወይም ትራንዛሽኖች የተፈጸመ ነው፡፡ ይህ አፈጻጸም ከቀዳሚው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር፣ በግብይት የ35 በመቶ በገንዘብ መጠን ደግሞ የ118 በመቶ ዕድገት የታየበት ነው፡፡

በቀዳሚው ዓመት በሙሉ የሐሳብ ዓመት 3.2 ትሪሊዮን ብር ማንቀሳቀስ ችሎ የነበረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ የስድስት ወራት 2.8 ቢሊዮን ብር ማንቀሳቀስ የቻለው ከ12 ሚሊዮን በላይ የኤቲኤም ተጠቃሚ፣ ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የሞባይል ባንክና ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ በሚሆኑ ደንበኞች በመያዝ እንደሆነ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሌሎች ባንኮች የተለየ ይህንን አገልግሎት ማስፋት የቻለው፣ በተለይ ከ2013 ሐሳብ ዓመት ወዲህ በአገልግሎቱ ዙሪያ ባካሄደው ማስፋፊያ ነው፡፡ ይህም የማስፋፊያ ፕሮጀክት በ2013 የሐሳብ ዓመት ከግማሽ ትሪሊዮን ብር በላይ ማድረስ አስችሎታል፡፡ እንደ ብዙዎች ባንኮች በሞባይል ባንክ አገልግሎት ከፍተኛ ገንዘብ ያንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በሞባይል ባንኪንግ ብቻ 2.4 ትሪሊዮን ብር በሞባይል ገንዘብ ማዘዋወር ተችሏል፡፡ በኤቲኤም ማሽን ደግሞ 308 ቢሊዮን ብር፣ በኢንተርኔት ባንኪንግ 260 ቢሊዮን ብር፣ በሲቢኢ ብር 19 ቢሊዮን ብርና በፖስ ማሽን 17 ቢሊዮን ብር ግብይት ተከናውኗል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁሉ ሌሎች ባንኮችም በዲጂታል የባንክ አገልግሎት የሚያንቀሳቀሱት የገንዘብ መጠን እያሳደጉና አብዛኛውንም የገንዘብ እንቅስቃሴ በዚሁ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት እያካሄዱ መሆናቸውን እያመለከቱ ነው፡፡ ዲጂታል ባንክ አገልግሎት ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ለመምጣቱ የተለያዩ ምክንያቶች የሚጠቀሱ ሲሆን፣ በዋናነት ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴን ተግባራዊ ያደረገው መመርያ ተጠቃሽ ነው፡፡

የዲጂታል የገንዘብ እንቅስቃሴ መጠን ዕድገት መታየት የጀመረውም ከባንኮች በጥሬ ገንዘብ የሚወጣው እንዲገደብ ለማድረግ ነው፡፡ ከግንቦት 2012 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የተደረገው መመርያ በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ግብይትን ለመቀነስ አስችሏል፡፡

ይህ መመርያ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ ከባንኮች ይወጣ የነበረው ገንዘብ ገደብ አልነበረም፡፡ በመሆኑም በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ክፍያ ላይ ገደብ በመጣል ለግሰለብ መጀመሪያ በቀን እስከ 200 ሺሕ ብር፣ በወር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ጥሬ ገንዘብ ማውጣት የሚቻልና ከዚያ በላይ ያለውን ገድቧል፡፡ ለኩባንያዎችም በቀን እስከ 300 ሺሕ ብርና በወር እስከ 2.5 ቢሊዮን ብር ድረስ ብቻ ማውጣት እንደሚቻል ደንግጓል፡፡

ይህ መመርያ ግን እንደገና ተሻሽሎ ለግለሰብ እስከ 50 ሺሕ ብር ዝቅ ብሏል፡፡ ለኩባንያዎችም እስከ 100 ሺሕ ብር እንዲሆን ተወስኖ፣ ከዚህ በላይ ገንዘብ ማንቀሳቀስ ከተፈለገ ግን ዲጂታል የባንክ አገልግሎት ከአካውንት ወደ አካውንት ማስተላለፍ ወይም በሌሎች እንደ ቼክ መሰል አገልግሎት እንዲጠቀሙ ማስገደዱ ለዲጂታል የገንዘብ ዝውውሩ ዓይነተኛ ሚና አለው፡፡

ሌላው ምክንያት መንግሥት ከፍተኛ የገንዘብ ልውውጦች የሚደረግባቸው ግብይቶች በዲጂታል የባንክ አገልግሎት እንዲከናወኑ በመወሰኑ ወደ 200 የሚጠጉ የመንግሥት ኩባንያዎች በዚህ አሠራር ውስጥ እንዲያልፉ መደረጉ ነው፡፡ በዓመት ከ200 ቢሊዮን ብር በላይ ግብይት ይፈጸምበታል የተባለው የነዳጅ ግብይትና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎች በአስገዳጅነት በዲጂታል ክፍያ እንዲፈጽሙ መደረጉ ለዕድገቱ በተጨባጭ አስተዋጽኦ እያደረጉ ነው፡፡

ዲጂታል የባንክ አገልግሎትን ለማቀላጠፍ አጋዥ ይሆናሉ ከተባሉ መተግበሪዎች መካከል አንዱ የሆነው ኤ ቲ ኤም ሲሆን፣ በ2015 የሐሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ባንኮች በመላ አገሪቱ 7,858 የኤ ቲ ኤም ማሽኖች ሥራ ላይ መዋላቸውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መረጃ ያመለክታል፡፡

አውቶሜትድ ገንዘብ መክፈያ (ፖዝ) ማሽኖች ቁጥር ደግሞ ከ12 ሺሕ በላይ መድረሳቸውን ያመለክታል፡፡ በእነዚህ ማሽኖች የተደረገው የገንዘብ ዝውውር ደግሞ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መምጣቱንም ይጠቁማል፡፡ እንደ መረጃው ሥራ ላይ ባሉት የኤ ቲ ኤም ማሽኖች በ2015 የሐሳብ ዓመት ብቻ ከ356.3 ሚሊዮን በላይ በሆነ ሁኔታ ከ478.3 ቢሊዮን ብር በላይ መንቀሳቀስ ተችሏል፡፡ በፖዝ ማሽኖች ደግሞ ከ6.6 ሚሊዮን በሚሆን ትራንዛክሽን ከ40.8 ቢሊዮን ብር በላይ ክፍያ መፈጸም መቻሉን ያሳያል፡፡

በእነዚህ የዘመናዊ ግብይትና የዲጂታል የገንዘብ እንቅስቃሴ መተግበሪያዎች የሚጠቀሙ ደንበኞች ቁጥር እያደገ መሄድ የገንዘብ እንቅስቃሴውም እንዲጨምር እያደረገ ነው፡፡ ባለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት መረጃዎች እንደሚጠቅሱትም፣ የተገልጋዩን ፍላጎት መጨመር ተከትሎ የኤቲኤም ማሽን ቁጥሮች በየዓመቱ እየጨመረ ነው፡፡

በ2013 ሐሳብ ዓመት የኢትዮጵያ ያሉ የኤቲኤም ማሽኖች 9,208 የነበረ ሲሆን፣ ይህም ቁጥር በ2014 ሐሳብ ዓመት ወደ 11,760 ሊደርስ ችሏል፡፡ የፖስ ማሽኖችንም ቁጥር በ2013 የሐሳብ ዓመት 6,343፣ በ2014 ደግሞ ወደ 6,902 በማደግ፣ በ2015 ሐሳብ ዓመት መጨረሻ ላይ ወደ 7,878 ሊደርስ ችሏል፡፡ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት በዚህን ያህል ደረጃ እያደገ መምጣት ባንኮችና ሌሎች አገልግሎቱን የሚሰጡ ተቋማት ገቢን እየጨመሩ መሆኑም ይታመናል፡፡ በእያንዳንዱ የገንዘብ ዝውውር እየተጠየቀ ያለው የአገልግሎት ክፍያ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መጨመር ከዋና ዋና ባንኮች ገቢዎች መካከል አንዱ ወደ መሆን ተሸጋግረዋል፡፡

የዲጂታል የባንክ አገልግሎት አሁን የደረሰበት ደረጃ ይህንን ቢመስልም የአገልግሎት ክፍያው ግን ጥያቄ ማስነሳቱ አልቀረም፡፡ በተለይ ከአንድ ባንክ ወደ ሌላ ባንክ የሚደረግ የገንዘብ ዝውውር ላይ እየተጠየቀ ያለው የአገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ ነው የሚሉ የደንበኞች አስተያየት ጎልቶ እየተሰማ ነው፡፡ አንድ ደንበኛ ከሆነበት ባንክ ገንዘብ ሲያንቀሳቅስ እየተከፈለ ያለው የአገልግሎት ዋጋ ፍትሐዊ አይደለም የሚሉ ተጠቃሚዎች በተለይ የገንዘብ መጠኑ በጨመረ ቁጥር ለአገልግሎቱ የሚከፍሉት የገንዘብ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

ከራስ ባንክ በኤ ቲ ኤም ገንዘብ ለማውጣት በአንድ ሺሕ ብር ሁለት ብር የአገልግሎት እየተቆረጠ ነው፡፡ ከባንክ ወደ ሌላ ባንክ ገንዘብ ለማዘዋወርም በአንድ ሺሕ ብር አምስት ብር ይከፈላል፡፡ ይህ የአገልግሎት ዋጋ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከ50 ሳንቲም እስከ አንድ ብር የሚከፈልበት የነበረ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተደረገው ጭማሪ ከፍተኛ ሊባል የሚችል እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

የዲጂታል የባንክ አገልግሎት በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ዕድገት ያሳየበት አንዱ ምክንያት ባንኮች ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለአገልግሎቱ አጋዥ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ማካሄዳቸው ነው፡፡ በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት ማቅረብ ግድ በመሆኑ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በዚህ ረገድ ብዙ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ያሉ ተቋማት በሞባይል የባንክ አገልግሎት ዘርፍ እያከናወኑ ያሉ እንቅስቃሴዎች ግን በዲጂታል ባንክ አገልግሎት ለመስፋፋት ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡

በባንክ ኢንዱስትሪው ውስጥ የረዥም ዓመት ልምድ ያላቸው የባንክ ባለሞያዎች ሲናገሩ፣ የዲጂታል የባንክ አገልግሎት ለተገልጋዩም ሆነ ለባንኮች እጅግ ጠቃሚ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ተገልጋዩ በቀላሉ ገንዘብ በማንቀሳቀስና ክፍያዎችን መክፈል እያስቻለው ነው፡፡ «ባንኮች ወደ ዲጂታል የባንክ አገልግሎት እያዘነበልን ያለነው ወጪን ለመቀነስ ነው፤» ይላሉ፡፡በአሁኑ ወቅት አንድ ቅርንጫፍ ከፍቶ አገልግሎት መስጠት ባንኮችን ለከፍተኛ ወጪ እንደሚዳርግ በመሆኑም ባንኮች የዲጂታል የባንክ አገልግሎታቸውን ማስፋፋት ተመራጭ እያደረጉ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

አሁን የዲጂታል ባንክ አገልግሎት መተግበሪያዎች ተደርገው ከሚወሰዱት የተለያዩ አማራጮች ውስጥ አንዱ ኤ ቲ ኤም መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ አሁን እየታየ ካለው የሞባይልና የኢንተርኔት የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር ዕድገት አንፃር፣ የኤ ቲ ኤም ድርሻ እየቀነሰ የሚሄድ ስለመሆኑም ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡ በመሆኑም ዲጂታል የባንክ አገልግሎትን ከማስፋት አንፃር የሞባይል ኢንተርኔት ባንኪንግ አገልግሎት የዲጂታል ባንክ አገልግሎቱ ዋነኛ መሣሪያ ሆነው እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል፡፡

ከዲጂታል የባንክ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከዚህ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ አሁን ያለው ትልቁ ችግር ሳይበር ሴኪውሪቲ ነው ፡፡ ብዙ የማጭበርበር ሙከራዎች ይኖራል፡፡ ስለዚህ ይህንን ሥጋት ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች ለባንኮች ተግዳሮት ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው፡፡ ሌላው በዘርፉ ያለው ተግዳሮት ቴክኖሎጂው በጣም ወጪ የሚጠይቅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለሳይበር ሴኪውሪቲ የሚወጣው ወጪ ደግሞ አጠቃላይ ወጪውን የበለጠ ያንረዋል ቢሆንም ግን ዘመናዊነትን ለማምጣትና ከቱሩፋቶቹ ለመቋደስ ለችግሮቹ ተባብሮ መፍትሄ መፈለግ ይገባል።

# በኤች አይ ቪ . . .

ከገጽ 6 የዞረ

ሌሎች ማህበራዊ ክንዋኔዎች ያለ ችግር መፈፀም ያስችለዋል፡፡

የኤች.አይ.ቪን በግብረ ስጋ ግንኙነት ወደ ትዳር አጋር ወይም ፍቅረኛዉ የማስተላለፍ እድሉ የተገታ ይሆናል፡፡ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ ህክምና ታካሚ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የቫይረስ ልኬት ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እየወሰደ ያለዉ መድሃኒት የቫይረሱን መጠን በምን ያህል እየቀነሰ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

የፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒት በመውሰድ ላይ ያለ ታካሚ የሚከተሉትን ማወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል፡፡ በቫይረስ ልኬት ምርመራ ውጤት የቫይረሱ መጠን አይታይም ማለት ቫይረሱ ጠፍቷል፤ ወይም ታካሚዉ ከኤች.አይ.ቪ ነፃ ነው ማለት አይደለም፡፡ የቫይረሱን በማይታይበት ደረጃ ለማስቀጠል ታካሚዉ ጠንካራ የመድሀኒት ቁርኝት ሊኖረዉ ይገባል፡፡

በተገኘው የቫይረስ ልኬት ምርመራ ውጤት በመርካት ወይም በሌላ ምክንያት የሚከታተለዉን መድሃኒት መዉሰድ ከተወ በሰውነት ውስጥ ያለው የቫይረስ መጠን መልሶ እንዲጨምርና ላልተፈለጉ የጤና ችግሮች የመጋለጥ ዕድል ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

ዝቅተኛ የቫይረስ ልኬት ምርመራ ውጤት ወደማይታይ ደረጃ ሁሌም መድሃኒቱን በአግባቡ መዉሰድ እና ወቅቱን ጠብቆ የቫይረስ ልኬት ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የማይታይ የቫይረስ መጠን የደረሰ ታካሚ የኤች.አይ.ቪ መከላከል ጥንቃቄዎችን (ታማኝ መሆን ወይም ኮንዶም መጠቀም ) ማድረግ አለበት፡፡

ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመከላከል ፕሮግራም (Pmtct) ኤች.አይ.ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍን ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት እናቶች የቅድመ ወሊድ አገልግሎት፣ የወሊድ አገልግሎት እና የፀረ-ኤች.አይ.ቪ መድሃኒትን በአግባቡ መከታተል እንዲሁም ጡት በማጥባት ወቅት የጤና ባለሞያ ምክር በመከተል እና ተያያዥ የህክምና አገልግሎቶችን በመጠቀም ከቫይረሱ ነፃ የሆነ ልጅ ወልዶ ማሳደግ ይቻላል፡፡

ከሌላዉ ፕሮግራሙ አፈፃፀም አናሳ መሆን የሚጠቀሰዉ ምክንያት የባሎች ተሳትፎ አናሳ መሆኑ ነዉ፡፡ በ2014 ዓ.ም ምርመራ ከመጡ ነፍስጡር እናቶች የትዳር አጋራቸዉ አብሯቸዉ ለምርመራ ወደ ጤና ተቋም የመጡ ባሎች 24% ብቻ ናቸዉ፡፡ ከኤች.አይ.ቪ ነፃ ትዉልድ ለማፍራት የባሎችም ተሳትፎ ትልቅ አስተዋፆ አለዉ፡፡

የአባላዘር በሽታ ምርመራ እና ህክምና አገልግሎት የአባለዘር በሽታ ምልክቶች በታየ ጊዜ በወቅቱ ምርመራ በማድረግ ህክምና ካልተደረገ በኤች.አይ.ቪ የመያዝን እድል በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል፡፡ የአባላዘር በሽታ ምልክንያቶች በታየ ጊዜ በአፋጣኝ እራሶን እና ፍቅረኛዎትን/የትዳር አጋሮን/የወሲብ ተጓዳኞት ህክምና ማስጀመር አለቦት፡፡ በ2014 ዓ.ም ለዓባላዘር ህክምና ወደ ጤና ተቋም መጥቶ ህክምና መዉሰድ ካለባቸዉ ሰዎች 43% ያህል ብቻ ነዉ ህክምናዉን የወሰዱት፡፡

የአባላዘር ህክምና ሽፋን በሚፈለገዉ መጠን ከፍ እንዳይል ከሚያደርገዉ ምክንያቶች አንዱ እና ዋነኛዉ በማህበረሰባችን ዉስጥ ስለ አባላዘር በሽታ ያለዉ የተሳሳተ አመለካከት ነዉ፡፡ በማህበረሰባችን ዉስጥ ያለዉን የተሳሳተ አመለካከት በማስተካከል የበሽታዉ ምልክት የታየባቸዉ ሰዎች ከልማዳዊ አመለካከት ይልቅ በአፋጣኝ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ ህክምናዉን በመከታተል መዳን እንደሚቻል በማሳወቅ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ማሳደግ ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ ማህበረሰቡ የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶች ተደራሽነታቸዉን ማረጋገጥ (በተለይ ለይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች) ወጣቶችን (በት/ቤት እና ከት/ቤት ዉጭ ያሉ) ለኤች.አይ.ቪ አጋላጭ ከሆኑ ባሃሪ እንዲታቀቡ እና አዎንታዊ ባህሪ እንዲያዳብሩ ማገዝ አድሎ እና መገለልን ማስቀረት (በማህበራዊ ህይወት፤ በስራ ቦታ፤ ወዘተ) ኤች.አይ.ቪ በደማቸዉ ያለባቸዉ ወገኖች አስፈላጊዉን እገዛ ማድረግ ይገባል፡፡

በየደረጃዉ ያለ አመራር ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት መንስዔዉ ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ እና የሚያስከትለዉም ተፅዕኖ ብዙ ከመሆኑ አንፃር፤ ቫይረሱን ለመከላከል የሚደረገዉ ጥረትም ዘርፈ ብዙ መሆን ይኖርበታል፡፡ በየደረጃዉ ያለ አመራርም ይህን ከግንዛቤ በማስገባት ለዘርፈ ብዙ ኤች.አይ.ቪ ምላሽ አስፈላጊዉን ትኩረት መስጠት፤ በቂ በጀት መመደብ እና የፕሮግራሞችን ተፈፃሚነት ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

የሲቪክ ማህበራት ለኤች.አይ.ቪ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ትኩረት በመስጠት የኤች.አይ.ቪ ፕሮግራሞችን ተደራሽ ማድረግ፡፡ የአድሎ እና መገለልን ለማስቀረት ማህበረሰቡን ማስተማር ወጣቶች ከኤች.አይ.ቪ እራሳቸዉን እንዲከላከሉ ማብቃት እንዲሁም የጤና ባለሞያዎች የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አገልግሎቶችን ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ያለምንም አድሎ መስጠት ለኤች.አይ.ቪ ይበልጥ ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ትኩረት አድርጎ የመከላከል አገልግሎት መስጠት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመከላከል ከእኔስ ምን ይጠበቃል? ብሎ መነሳት ያስፈልጋል፡፡

# የዋጋ ንረቱን . . .

ከገጽ 1 የዞረ

በድሬዳዋ አስተዳደር ገበያውን ለማረጋጋት እና መሠረታ የፍጆታ እቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የሸማች ኅብረት ስራ ማኅበራት ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተጠቅሶ የሸማች ኅብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በልዩ ትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ የአስተዳደሩ ምክትል ከንቲባና ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሐርቢ ቡህ ገልፀዋል።

አቶ ሐርቢ ቡህ አክለው በአስተዳደሩ በሚቀርቡ የመሠረታዊ የፍጆታ እቃዎቾ ላይ የምርት እጥረት እንዳይከሰት ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የምግብ እና የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ከተለያዩ ክልሎች ወደ አስተዳደሩ በማስገባት ከሸማች ኅብረት ስራ ማህበራት ጋር የገበያ ትስስሮችን በመፈጠር ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ፍስሃ ይታገሱ በበኩላቸው በምርት አቅርቦትና ስርጭት ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ደረጃ የሚፈቱ ችግሮች በመለየት እንደሚሰራ ገልፀዋል።

በጉብኝቱም ዕለት እንደተጠቀሰው ከማምረቻና ከመሸጫ ቦታ ችግሮች ፣ ከግምሩክ እና ከቀረጥ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ክፍተቶችና ችግሮችን ለመቅረፍም ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ከቢሮውና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እንደሚሰራ ተገልጿል ።

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር የተመራው ልዑክ ቡድን የ02 እና 08 ወረዳ የሸማች ኅብረት ስራ ማህበራት፣በረከት የጨው ፋብሪካ እንዲሁም በፍራንኮቫሉታ የተፈቀደላቸው ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴዎች የስራ እንቅስቃሴ ተዘዋውረው የጎበኙ ሲሆን በየወረዳው የሚገኙ የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች የስራ እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል ።

**መረጃ:-ን/ኢ/ኢ/ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ክፍል**

## የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬዳዋ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ፑል በሥሩ ለሚገኙት ለመንገዶች ባለስልጣን ለ2016 በጀት ዓመት ለከባድና ቀላል መኪኖች የሚሆን ጎማ ና ካለመዳሪና ፍላፕ እና ለሞተር ሳይክል (ተሽከርካሪዎች የጎማ ግዥ ለመፈፀም ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በግልፅ ጨረታ እንዲወዳደሩ ይጋብዛል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን መስፈርት የምታመሟሉ ተጋብዛችኋል፡፡

በጨረታው መወዳደር ለሚፈልጉ ተሣታፊዎች የጨረታው መስፈርት፡-

1.በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸው

2.የዘመኑን ግብር የከፈሉ

3.የቫት ተመዝጋቢ ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ

4.የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው

5.የአቅራቢነት ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችል

6.የጨረታ ማስከበሪያ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በጥሬ ወይም CPO ማስያዝ ይኖርበታል

7.ተጫራቾች የሚጫረቱባቸውን ሠነዶች ዋጋ በመሙላት በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማሸግ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

8. ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት አየር ላይ ውሎ በ16ተኛ ቀኑ ይከፈታል፤የጨረታ ሰነዱን 300 ብር በመክፈል ፋይናንስ ክፍል መግዛት ትችላላችሁ፡፡

9.ጨረታውን ሞልታችሁ የመለሳችሁ እለት በእዛው ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ታሽጎ በዛኑ ዕለት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ግዥ ክፍል 4፡00 ይከፈታል፡፡

10.መ/ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሠነድ ላይ ዋጋ እንዲሁም በአቅራቢነት መሞላት ያለበት የዶክመንት ክፍል ሞልተው የድርጅታቸውን ማህተም በማድረግ እንድታቀርቡ እያሳሰብን በመመሪያው መሰረት የማያቀርቡ ተጫራች ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ማሣሰቢያ፡-መ/ቤቱ በጨረታው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ ከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ የስ/ቁ 09 15 75 53 24

አድራሻ፡- ድሬደዋ ከተማ ሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ቢሮ ትራፊክ መብራት አጠገብ ከቴሌ ህንጻ ከፍ ብሎ፡፡

## ማስታወቂያ

ጨረታው በ02/08/2016ዓ.ም. የወጣ እና በድጋሚ የተስተካከለ ነው

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት የአየር ንብረት ለውጥ እና ኢነርጂ ተደራሽነት የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት ይፈልጋል በዚሁ መሰረት አማካሪ ድርጅቶችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም፡-

1.ጨረታ መለያ ቁጥር 06/2016

2.ግብር ክፍያ መለያ ቁጥር /TIN No/ያለው

3.ቫት ወይም TOT ተመዝጋቢ የሆነ

4.የዘመኑን የ2016 ግብር የከፈለበት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል

5.ለጨረታ ማስከበርያ ብር 10000 ብር በባንክ በተረጋገጠ CPO ማስያዝ የሚችል

6.መንግስት ግዥ ለመሳተፍ የሚችል ስርተፊኬት ያለውና ማቅረብ የሚችል፡፡

7.ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር ) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ለዚህ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ፡፡

8.ጨረታውን በ11ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡00 ሰአት ይዘጋና ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎች በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሰአት ይከፈታል፡፡

ፅ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው

ለተጨማሪ ማብራሪያ

በስልክ ቁጥር 0915169958 ታጁዲን አብዱላሂ በመደወል መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ

በድሬደዋ አስተዳደር የቀበሌ 03 አስተ/ጽ/ቤት በ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት

ሎት 1፡- የስፖርት ትጥቅ እቃዎች

በግልጽ ጨረታ አወዳደሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በዘርፉ የተሰማሩ የሚከተለውን መስፈርት የሚያሟሉ ድርጅቶችን አወዳድሮ ማጫረት ይፈልጋል፡፡

1ኛ.በተጠቀሰው የስራ ዘርፍ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያለውና የዘመኑን ግብር የከፈለ፡፡

2ኛ. በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገበና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፡፡

3.ኛ. ተጫራቶች የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ ለእያንዳንዱ ሎት ብር 3000/ ሶስት ሺ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይንም ሲፒኦ የመወዳደሪያ ዋጋቸውን አያይዘውና አሽገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

4ኛ.ተጫራቾች ይህ ጨረታ በድሬ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታተይ ቀናት የጨረታ ሰነዱን በቀበሌ 08 ጽ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 10 በብር 300.00 መግዛት ትችላላችሁ፡፡

5ኛ. የጨረታው መከፈቻ ቀን በእረፍት ቀን ወይም በበአላት ቀን ላይ ከዋለ በቀጣዩ የሥራ ቀን ይከፈታል፡፡

6ኛ.አሸናፊ ተጫራች ሆኖ የሚገኝ ማሸነፉ በተገለጸለት ቀን ከግዢ አካል ጋር ውል መፈጸም የሚችል እና በውል መፈጸምያ ወቅት 10/100 ውል ማስከበሪያ ማቅረብ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

8ኛ. ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት ህጋዊ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዕለቱ 3፡00 ሰዓት ተዘግቶ 3፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡

9ኛ. ከጨረታ መከፈቻ ቀንና ሰዓት በኋላ ዘግይቶ የሚመጣ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

10ኛ. ቢሮው የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ፡-

የቀበሌ 03 አስተዳደር ጽ/ቤት የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

በስልክ ቁጥር 0915002937 ወይም 0933331217 መነጋገር ይችላሉ፡፡

## በድጋሚ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ለ2016 በጀት ዓመት የተሽከርካሪ ጥገና ለማድረግ ከዚህ በታች በቀረቡት መስፈርቶች መሰረት ጨረታ አዉጥቶ ተጫራቾችን ለማወዳደር ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም

1. ጨረታ መለያ ቁጥር 005 /2016
2. ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN NO/ ያለዉና ማቅረብ የሚችል
3. የቫት ተመዝጋቢ የሆነና ማስረጃ ማቅረብ የሚችል
4. የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማሰረጃ ማቅረብ የሚችል
5. የአቅራቢነት ምስክር ወረቀት ማስረጃ ማቅረብ የሚችል
6. ለጨረታ ማሰከበሪያ ብር 10,000/ አስር ሺ ብር/በባንክ በተረጋገጠ cpo ማሰያዝ የሚችል፡፡
7. ኢንሹራንስ ያለው መሆን አለበት
8. በቂ የመኪና ማቆሚያ እና ሰራተኛ ያለው ማሳየት የሚችል
9. የጨረታ ሠነዱን በድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት የግዥ/ንብ/አ/ዳይሬክቶሬት

በመቅረብ የጨረታ ሰነዱን በብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ መግዛት የምትችሉ ሲሆን ይህ ማሰታወቂያ በጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 /አስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ዉሰጥ ለዚህ በተዘጋጀዉ የጨረታ ሳጥን ዉሰጥ ማሰገባት ይችላሉ፡፡

10. ጨረታዉ በ16ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 3፡30 ሰአት ይዘጋና ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሰአት ይከፈታል

11. ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታዉን በመሉ ሆነ በከፊል መሰረዝ የሚችል መሆኑን አናስታዉቃለን፡፡

ለተጨማሪ ማብራሪያ

በስልክ ቁጥር 025 112 13 62 በመደወል መጠየቅ ይችላሉ

## Invitation to Bid

Place and Date: Dire Dawa, Apri1, 2024

Procurement Reference Number:DDA/CPDA/001/2016

1.The D.D.A.Community Participation and Development Ajency having legal address at;

| | |
|---|---|
| P.O.Box; | 963 |
| Street Adress; | Kebele 04 |
| Town/City; | Dire Dawa |
| Telephone; | 0963948902 |
| Fax; | 0254110898 |

2.The D.D.A.Community Participation and Development Ajency now invites sealed bids from eligible and qualified bidders for;Costruction of Walkway steps and ditch work (LOT 2)(location ;kebele 04,Dire Dawa)

3.Intended Completion Date for the whole of the Works shall be 60calendar days.

4.Bidding will be conducted through open local contained in public proclamation of FDRE and is open to all Eligible bidders.

5.Interested eligible bidders may obtain further information from D.D.A.Community Participation and Development Ajency and inspect the bidding documents at the address given below from 7:30 – 12:00 AM& 2:00 – 5:30 PM working hours.

6.Qualifications requirements include: Contractors of category GC/BC-10, 9, 8 & 6 (who has served in diredawa city administration in engineering proffesion earned competence certificate for- category -6 Furthher more ,Contractors are required to submit Evidences provided in obtaining Category- 6 Certificate of Compitence ) Only with license valid for the year 2016 E.C. No work Experience is required.

7.A complete set of Bidding Documents in English may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non-refundable fee of ETB 500 in Cash.

8.Bidders shall submit their bids in two envelopes,the first envelope labeled as Qualification Information and bid security and second envelop Financial bid, separatly sealed and the two encelopes sealed in on another outer enveiope.Evaluation is to be carried out in two stages .Technicians Proposal first and Financial proposal of qualified bidders next.

9.Bids must be delivered to the address belowat or before 9:00 AMOn the 15th Date from the Date of Announcement. Late bids will be rejected.

10.Bids Will Be Opened In The Presence Of Bidder's Representatives Who Choose To Attend At The Same Date Of Submission At 9:30 AM

11.All bids must be accompanied by a Bid Security of ETB25,000 (Twenty Five Thousand Ethiopian Birr only) in the form of Cash, an Unconditional Bank Guarantee or CPO.TheBid Security shall be valid for 28 days beyond the validity of the Bid.

12.The public body reserves the right to reject any bid and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award, without thereby incurring any liability to Bidders.

13.The address referred to above is:

| | |
|---|---|
| Public Body | D,D A Cmmunity Participation and Development Agency |
| Athorized Representative | Gelan Mohammed |
| Telephone Number; | 0254-119204/0898 |
| P.O.Box | |
| Street Address; | Kebele 04 |
| Town/City | Dire Dwa |

## ማስታወቂያ

ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ቢሮ በሥሩ በሚገኘው ኮንስትራክሽን ሬጉላቶ እና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሥራዎች መሠማራት ለሚፈልጉ ከሚሠጣቸው አገልግሎቶች መካከል ለኮንስትራክሽንና ለዲዛይን ባለሙያዎች የሙያ ምስክር ወረቀት ለሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎችብቃት ማረጋገጫ እየሰጠን መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ሆኖም ከሚያዚያ 07 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ግን የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ በመመሪያ ቁጥር 01/2007 እና በመመሪያ ቁጥር 02/2007 ተሸሮ አዲስ የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 4/2016 ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም ከሚያዚያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ግን የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ በመመሪያ ቁጥር 01/2007 እና በመመሪያ ቁጥር 02 /2007 መሠረት ስንሰጣቸው የነበሩትን ለኮንስትራክሽንና ለዲዛይን ባለሙያዎች የሙያ ምስክር ወረቀት ለሥራ ተቋራጮችና አማካሪዎችብቃት ማረጋገጫ የአገልግሎት አሰጣጥ የተቀየረ መሆኑን እየገለፅን ከሚያዚያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ ተሻሽሎ በተዘጋጀው የኮንስትራክሽን ብቃት ማረጋገጫና ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 4/2016 መሠረት ቀድሞ ስንሰጣቸው የነበሩት አገልግሎቶች እና ተጨማሪ ከ30 የኮንስትራክሽን ሙያ ዓይነቶች በላይ የልዩ ሥራ ተቋራጮና ልዩ አማካሪ ብቃት ማረጋገጫ እና የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ምዝገባ አገልግሎት መስጠት የምንጀምር መሆኑን እንገልፃለን፡፡

# በዲያስፖራ. . .

ከገጽ 1 የዞረ

እና ወዳጆች ለከተማዋ ኢኮኖሚ እድገት አስተዋፆ እንዲያደርጉ መቻሉንም ነው አቶ ሀርቢ ቡህ የተናገሩት ፡፡

ዲያስፖራው በኢትዮጲያ ፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ በቂ እውቀት ያለመኖሩ በተለይም በዲያስፖራ ጉዳዮች አስተዳደራዊ እንቅስቃሴዎች እና የኢንቨስትመንት ቦታ ጥያቄ ላይ ችግር በመፍጠሩ ፣ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለዲያስፖራው ማህበረሰብ ቤተሰቦች ግንዛቤ መፍጠር እና የሚላከውን ሪሚታንስ ፈጥኖ በኢኮኖሚው ውስጥ አቅም እንዲፈጥር አለማድረጉና ሌሎች ተያያዥ ተግዳሮቶች በህግ ተለይተው የተሰጡንን ተግባር እና ሀላፊነቶች አፈፃፀምን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ተግዳሮት የሆነውን ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የምክክር መድረኩ መካሄዱን የድሬዳዋ አስተዳደር የዲያስፖራ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ቢኒያም ግርማ ተናግረዋል ፡፡

በመርሀ ግብሩ ላይም በዳያስፖራ የኢንቨስትመንትና የቤት ልማት ፓኬጅ ቀረፃ ዙሪያ የዲያስፖራ የንግድና ኢንቨስትመንት አስተባባሪ የሆኑት አቶ ጀማል ዑመር ሰነድ አቅርበዋል ፡፡

**በአለማየሁ አበበ**

# የማቲዎስ ወንዱ - የካንሰር ሶሳይቲ የ20 ዓመት ጉዞ

ከመሪር ሃዘን ውስጥ የተወለደ በጎነትና ብርታት

ማቲዎስ ወንዱ-የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ፤ መሪር ሃዘንን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር፣ በልጅ ፍቅር ሳቢያ የተቋቋመ የካንሰር ድርጅት ሲሆን፤ ማህበሩ ከተመሰረተ ሁለት አስርት ዓመታትን አስቆጥሯል። በአሁኑ ሰዓትም ማህበሩ የተመሰረበትን የ20ኛ ዓመት ክብረ በዓል እያከበረ ነው።

ማቲዎስ ወንዱ፤ የአቶ ወንዱ በቀለና የወ/ሮ አምሳለ በየነ ሦስተኛ ተወዳጅ ልጃቸው ነበር - የአብራካቸው ክፋይ፡፡ ከአንድ ወር ዕድሜው ጀምሮ የማቲዎስ ሞግዚት የነበረችው ይፍቱሥራ ስለህጻኑ ስትናገር፤ “... ቆንጆ፣ ደስተኛ፣ ንቁና ጤናማ ልጅ ነበር። ዕድገቱም እንዲሁ ነው። ከዕድሜው በላይም ፈጣን- ያየው ሁሉ የሚገረምበት። እያደገ ሲመጣ ደግሞ የበለጠ ተወዳጅ እየሆነ የመጣ...” ትላለች፡፡

ህጻኑ የሁለተኛ ዓመት ልደቱን ባከበረ ማግስት ግን ማንም ባልጠበቀው ከባድ ህመም ተያዘ። የሆነው ሁሉ ለቤተሰቡ ዱብዳ ነበር። ሃኪሞች ህፃኑ በደም ካንሰር መታመሙን አሳወቁ። “ያን ቀን ቤተሰቡ ውስጥ የተፈጠረው ድንጋጤ መቼም አይረሳኝም። እኔ ካንሰር ሲባል የእኛ ሃገር ህመም አይመስለኝም ነበር። እንዴት ሊሆን ይችላል? በተለይ እናቱ የሆነችውን አሁን ሳስበው ለራሴም ይከብደኛል።” ትላለች የህፃኑ ሞግዚት፡፡

ማቲዎስ ለሁለት አመት ያህል በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ህክምና ሲከታተል መቆየቱን ቤተሰቦቹ ይናገራሉ፡፡ ከህመሙ እንደሚድን ተስፋ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም፣ ህመሙ አገርሽቶበት ወደ ውጭ አገር ሄዶ ህክምና ካላገኘ በስተቀር እዚህ አገር ተስፋ እንደሌለው የተነገራቸው ወላጆች ቤታቸውን ሸጠው ልጃቸውን ለማሳከም ይዘጋጃሉ፡፡ ማቲዎስ ዕድለኛ ሆኖ ግን ወላጆቹ ቤታቸውን ከመሸጣቸው በፊት በአሜሪካ የነጻ ህክምና ማግኘት ቻለ፡፡ ቤተሰብ ለአሜሪካ የህክምና ጉዞ ዝግጅቱን ጀመረ፡፡ ሆኖም ግን ከጉዞው በፊት የ4 ዓመቱ ተወዳጅ ህጻን ማቲዎስ ወንዱ ከዚህ ዓለም በሞት ተሰናበተ፡፡ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ሞግዚቱና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህክምና ክትትል ታደርግለት የነበረችውን ነርስ ጨምሮ መሪር ሃዘን ውስጥ ገቡ፡፡ ብዙ አዘኑ፡፡ ብዙ አለቀሱ፡፡

“ማቲዎስ ወንዱ በካንሰር ህመም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቱ ምክንያት ቤተሰቡ ላይ የደረሰውን እጅግ መራር ሃዘን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር፣ ማቲዎስን ማዳን ባይቻለን እንኳን፣ እጅግ ብዙ ማቲዎሶችን ለማዳን እንችላለን በማለት በ15 መሥራች አባላት የተመሰረተው



ሶሳይቲያችን፣ 20ኛ ዓመቱን ለማክበር በቅቷል።” ብለዋል፤ሚያዝያ 8 ቀን 2016 ዓ.ም በማርዮት ሆቴል መግለጫ የሰጡት የማቲዎስ አባትና የማህበሩ መሥራች አቶ ወንዱ በቀለ።

የማህበሩ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር የትናየት አበበ በበኩላቸው፤ ከዛሬ 20 ዓመት በፊት መሪር ሃዘን ወደ መልካም አጋጣሚ በመቀየር በተጀመረው ጉዞ፣ ዛሬ ሶሳይቲያችን ከ1ሺ 400 በላይ አባላት፣ ከ500 በላይ በጎ ፈቃደኞች እንዲሁም 300 ቋሚ ሰራኞችን በመያዝ፣ 8 ፕሮጀክቶችን በመተግበር ላይ ይገኛል።” ብለዋል።

የማህበሩን 20ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በታተመው “ፍርቱና” የተሰኘ መጽሄት ላይ የሶሳይቲው ዋና ዋና ዓላማዎች ተዘርዝረዋል። አንደኛው፤ የተሳሳተውን የካንሰር ገፅታ በመቀየር፣ ህብረተሰቡ ትክክለኛውን የካንሰር ምንነት፣ የመከላከያና መታከሚያ አማራጮቹን እንዲያውቅ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በአገራችን የካንሰር ህክምና ተሟልቶ የሚሰጥበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር፣ እንዲሁም አቅሙ ለሌላቸው አስፈላጊውን የሞራልና ማቴሪያል ድጋፍ መስጠት ሲሆን፤ ሦስተኛው፣ በአገራችን የሚገኙ የህክምናና የትምህርት ተቋማት በካንሰር ላይ ምርምር እንዲያደርጉ ማበረታታት የሚሉ ናቸው።

ከሁለት አስርት አመታት በፊት በማቲዎስ ወንዱ መኖሪያ ቤት የተመሰረተው የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ፣ በአሁኑ ወቅት ለካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸው ትርጉም ያለው ትብብርና ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል። ማህበሩ እስካሁን ድረስ ከ3ሺ በላይ የካንሰር ህሙማንና ቤተሰባቸውን መርዳቱ የተጠቆመ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት 175 የካንሰር ህሙማንና ቤተሰቦቻቸውን በመርዳት ላይ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።

ማህበሩ ለህሙማኑና ቤተሰባቸው ከሚሰጣቸው ድጋፎች መካከል ከአገራቸው የሚመጡበትና የሚመለሱበት ሙሉ የትራንስፖርት ወጪ፤ ሆስፒታሎች የማይሰጧቸውን መድሃኒቶች ከግል መድሃኒት ቤቶች እንዲገዙ ሲደረግ ሙሉ ወጪውን መሸፈን፤ የላቦራቶሪና ምርመራ አገልግሎቶች በግል ተቋማት ሲያሰሩ ሙሉ ወጪውን መሸፈን እንዲሁም ሆስፒታል ለህክምና በሚተኙበት ወቅት ለጥቃቅን ወጪ መሸፈኛ በወር 1ሺ ብር መስጠትና ሌሎችም ይገኙበታል- ተብሏል።

የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የፕሮግራም ዳይሬክተር አቶ ዘላለም መንግስቱ እንደሚገልፁት፤ ከ2006 ዓ.ም በኋላ የማህበሩ የፕሮጀክት ሥራዎች እየሰፉ የመጡ ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ የአሜሪካ ካንሰር ሶሳይቲ ፕሮጀክትን ይጠቅሳሉ። ካምፔይን ፎር ቶባኮ ፍሪ ኪድስ CFK) ከተባለው ድርጅት ጋር በመተባበር፣ በኢትዮጵያ የትምባሆ ቁጥጥር ህግ እንዲወጣ ማህበሩ እንቅስቃሴ ማድረጉንም አቶ ዘላለም ያወሳሉ።

“አሁን ስማችን ብቻ ነው ካንሰር ላይ ያለው” የሚሉት የፕሮግራም ዳይሬክተሩ፤ ከኮቪድ በኋላ ሙሉ በሙሉ ስትራቴጂያችንን ተላላፊ ያልሆኑ ህመሞች ላይ አድርገን ላቅ ያሉ ስራዎችን መስራት ችለናል ብለዋል። የሳንባ ካንሰር ፕሮጀክታችን ሌላ የካንሰር ህመም ዓይነት ላይ እንድንሰራ አስችሎናል ሲሉም አክለዋል- ዳይሬክተሩ።

አሳሳቢ የሚባል ደረጃ ላይ የደረሱት የማይተላለፉ ህመሞች፣ በአገራችን ከሚከሰት ሞት ውስጥ 52 በመቶውን የሚወክሉ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ማህበሩ በትኩረት እየሰራበት እንደሚገኝ ተነግሯል። በዚህም መሰረት ከግሎባል ኸልዝ አድቮኬ ሲ ኢንኩቤተር (GHAI) በተገኘ የገንዘብና ቴክኒክ ድጋፍ፤ ጠንካራ የሆነ ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ቁጥጥር አዋጅ በኢትዮጵያ እንዲፀድቅ ድጋፍ የሚሰጥ ፕሮጀክት ላይ እየሰራ ነው ተብሏል፡፡

ምንም እንኳን ማቲዎስ ወንዱ- የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ከተቋቋመ 20 አመታትን ቢያስቆጥርም፣ የዕድሜውንና እንቅስቃሴውን ያህል እንደማይታወቅ የሚናገሩት የማህበሩ የቦርድ አመራሮች፤ በዚህም ሳቢያ በብዙ ነገር መበደሉን ይገልጻሉ። አንዳንድ ማህበራትና ተቋማት በተመሰረቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ መሬት እያገኙ የራሳቸውን ህንጻ እንደሚገነቡ በማንሳትም፣ ማህበሩ ግን ለህመምተኞችና ቤተሰቦቻቸው መኖሪያ የቤት ኪራይ በዓመት ብዙ ሚሊዮን ብሮች በመክፈል ለህመምተኞች ድጋፍ ይውል የነበረ ገንዘብ ለኪራይ እያወጣ መሆኑን በቅሬታ ተናግረዋል - አመራሮቹ፡፡ በዚህ አጋጣሚም መንግሥት በተለይም የከንቲባ አዳነች አበቤ ቢሮ፣ ማህበሩ እየሰራ ያለውን በጎ ተግባር ገምግሞ ቦታ እንዲሰጠው ተማጽነዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት ማህበሩ ብዙ ተግዳሮቶችና ውጣ ውረዶች እንደገጠሙት እሙን ነው፡፡ የዚያኑ ያህልም በተለይ ባለፉት 5 ዓመታት ከተለያዩ ዓለማቀፍ ተቋማት በትንሹ 7 የሚደርሱ ሽልማቶችን ማግኘቱንም የሶሳይቲው መሥራች አቶ ወንዱ በቀለ ባለፈው ረቡዕ በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ተናግረዋል፡፡

በ4 ዓመት የጨቅላ ዕድሜው በካንሰር ህይወቱ ባለፈው ህጻን ማቲዎስ ወንዱ ስም የተቋቋመው ማህበር፤ የተመሰረተበትን 20ኛ ዓመት በዓል የሚያከብረው ለመተግበር በእጅጉ የሚፈታተኑ ትላልቅ ህልሞችና ፕሮጀክቶችን ከፊቱ ደርድሮ ነው -ከእነዚህም አንዱ የልህቀት ማዕከል ማቋቋሚያ ፕሮጀክት የሆነው “ጤናማ አፍሪካ- Healthy Africa” የተሰኘ ፕሮጀክት ነው ተብሏል፡፡

ምንጭ - አዲስ አድማስ ጋዜጣ

ከገጽ 12 የዞረ

## በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው የቦክስ ሻምፒዮና በኢትዮጵያ ጥሩ ውጤት ተመዘገበ




ለቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት እና የነፃነት ታጋይ ኔልሰን ማንዴላ ክብር በሚዘጋጀው የቦክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በተለያየ ሚዛን ካካፈለቻቸው አስራ ሶስት ቦክሰኞች ስድስት ሜዳልያዎች አገኘች።

ጋና በተደረገው የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች በቦክስ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ወርቅ ያስገኙልን ቤተልሄም ገዛህኝ እና ቤቴልሄም ወልዴ እንዲሁም ነህስ ያስገኘው ተመስገን ያሸንፋሉ ተብሎ ትልቅ ግምት የተሰጣቸው ቦክሰኞች ነበሩ።

በወንዶች ምክትል ሳጅን ተመስገን ምትኩ ማጣሪያዎቹን በዝረራ በመጨረስ ለፍጻሜ ደርሶ በሲሼልስ ተሸንፎ ብር ሜዳሊያ ያገኘ ሲሆን በሴቶች ቤተልሄም ገዛህኝ በደረሰባት የእጅ ውልቃት ምክንያት ጨዋታውን እየመራች ለማቋረጥ ተገዳ የብር ሜዳሊያ አግኝታለች።

እንዲሁም ሮማን አሰፋ ጥሩ ተፎካክራ የብር ሜድሊያ ተሸልማለች። በተጨማሪም በወንዶች ሱራፌል አላዩ እና ሚሊዮን ጨፀባ ነህስ ሜዳልያ ለሀገራችን ያስገኙ አትሌቶች ናቸው።

ባሳለፍነው ሳምንት የጀመረው እና ለተከታታይ ቀናት ሲደረግ ቆይቶ ፍፃሜውን ባገኘው ውድድር ላይ በመካፈል ዳጎስ ያለውን ሽልማት ለመውሰድ ሀምሳ አራት የአፍሪካ ሀገራት ደቡብ አፍሪካ ከትመው ነበር።

ከገጽ 12 የዞረ

## የአምናው እምባ እየታበሰ ነው

አርባ ምንጭ ከተማ የካ ክፍለ ከተማን 2ለ1 ማሸነፉን ተከትሎ ነጥቡን 54 አድርሷል። በሊጉ አንድ ጨዋታ ብቻ የተሸነፈው አርባ ምንጭ አራት ጨዋታዎች እየቀሩት ከተከታዩ አርሲ ነገሌ ጋር ያለውን የነጥብ ልዩነት ወደ 12 ከፍ አድርጓል። ይህ ደግሞ ከሞላ ጎደል ወደ ኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ መመለሱን የሚጠቁም ጉዞ ነው።

በ2015 የውድድር አመት የአርባ ምንጭ ከተማ እግር ኳስ ቡድን ወደ ከፍተኛ ዲቪዚዮን መውረዱን ሲያረጋግጥ የነበረው የሃዘን ድባብ በተለይም ደግሞ የአሰልጣኞቹ፣ የስራ አስኪያጁ እና የደጋፊው እምባ ከእግር ኳስ ቤተሰቡ አዕምሮ የሚጠፋ አይደለም።

በወቅቱ ከነበረው ጥልቅ ሃዘን በመነሳት በ2017 የውድድር አመት አዞዎቹ ወደ ሊጉ እንዲመለስ መልካም ምኞታቸውን የገለፁ በርካቶች ነበሩ። እነሆ ያ የብዙዎች ልባዊ ምኞች በአሰልጣኝ በረከት ደሙና በአጠቃላይ በቡድኑ አባላት እንዲሁም በአመራሮቹ ከፍተኛ ጥረት እውን ሊሆን ተቃርቧል።

ቡድኑ ወደ ከፍተኛ ሊግ መውረዱን ባረጋገጠ ግዜ ደጋፊው ጋር የነበረው የሞራል ስብራት የአመራሮቹን ልብ መንካቱ አልቀረም። ለዚህም ጥሩ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ቡድኑ መውረዱን ባወቀ በአጭር ግዜ ውስጥ የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ዳግም አርባ ምንጭ ከነማን እንዴት ወደ ሊጉ እንመልሰው ብለው መነሳታቸው ነው።

ይህን ለማሳካት ደግሞ የቡድኑን ቁልፍ ተጫዋቾች ለማቆየት የሄዱበት እርቀትና በበጀትና በሌሎች ግብአቶች ቡድኑ መጉላላት እንዳይገጥመው የተቻላቸውን ሁሉ ማድረጋቸው ነው። ቡድኑን ወደ ሊጉ ለመመለስ ብቸኛ አማራጭ አድርጎ ለተነሳ አመራር ወጣቱ አሰልጣኝ በረከት ደሙ ከቡድኑ ጋር እንዲቆይ መወሰናቸው ሌላው የአመራሩ ትልቁ ውሳኔ ነበር።



እሱም አላሳፈራቸውም የብዙዎች ድጋፍ ሳይዘነጋ አርባ ምንጭ ከነማን ወደ ሊጉ በመመለስ እንባ የተራጨውን ደጋፊ እንባ ሊያብስ አነሆ ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተውታል። የአርባ ምንጭ ከተማ አመራሮች ቡድኑ ወደ ፕሪሚየር ሊጉ እንዲመለስ ካደረጉት ጥረት ባሻገር አንድ ወጣት አሰልጣኝ በማብቃታቸው ምስጋና ይገባቸዋል።

አርባ ምንጭ ከተማ እግር ኳስ ክለብ በፕሪሚየር ሊጉ ተሳትፎ ባሻገር ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾችን በማበርከት የሚታወቅ ቡድን ነው። ታዲያ ይህ ዝነኛ ቡድን በቀጣይ የውድድር አመት በሊጉ ጠንካራ ተፎካካሪ ለማድረግ የክለቡ አመራሮች በረከት ደሙንና ሌሎች የአሰልጣኝ ቡድን አባላትን በምን መልኩ ማገዝ እንዳለባቸው ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ይህን ለማድረግ ደግሞ ግዜ ሳይወስዱ የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ከአሰልጣኞች ቡድን ጋር ሰፊ ውይይት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በዚህ ግዜ ባለፈው የውድድር አመት ቡድኑ በሊጉ መቆየት ያልቻለባቸውን ምክንያቶች በመገምገም ለ2017 የውድድር አመት ለግብአት መጠቀም ይቻላል።

## < <ለሁለንተናዊ እድገታችን ሠላም እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ትኩረት ሰጥተን ልንሰራበት ይገባል> >

### የዋሄል ወረዳ ነዋሪዎች

የድሬዳዋ ፖሊስ ሚድያ በዋሄል ወረዳ ስር የሚገኘው የለገ ኦዳ ጉዱንፈታ ፣ ሁሉል ሞጆ እና ዋሄል ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ላይ በመገኘት ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን ሠላም ለማረጋገጥ ከፀጥታ አካላት ጋር እያደረጉ ያሉትን ተሳትፎ በተመለከተ ቅኝት አድርጓል ።

ሰላም ለሁለንተናዊ እድገታቸው ወሳኝ መሆኑን በሚገባ የተረዱት የዋሄል የወረዳ ነዋሪዎች ለዚህ ስኬታማነት በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ስር የሚገኘው ከዋሄል ፖሊስ ጣቢያ ጋር በመሆን በተለይ በማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት አደረጃጀት አማካኝነት ሁሉም ነዋሪ እኔም የሰላም ዘብ ነኝ በሚል መሪ ቃል ለአካባቢው ሠላም መረጋገጥ እየሰሩ መሆናቸውን ተናግረዋል ።

ከድሬ ዳዋ ከተማ 36 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው የለገ ኦዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር በዋሄል ወረዳ ስር ከሚገኙ ዘጠኝ ቀበሌዎች መካከል አንዱ ስትሆን በተለይ የድሬዳዋ መግለጫ የሆኑና ከ7,000



ዓመታት በላይ እንዳስቆጠሩ የሚነገርላቸው የዋሻ ሥዕሎች የሚገኙበት እንደመሆኑ ቦታውን ለጎብኚዎች ምቹ ለማድረግ የመጀመሪያ ተግባር የአካባቢው ሠላም አስተማማኝ ማድረግ በመሆኑ በማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አገልግሎት አደረጃጀት አማካኝነት ማህበረሰቡ ራሱ በባለቤትነት የአካባቢውን ሠላም በመጠበቅ ላይ እንደሚገኝ የቀበሌው ነዋሪ እና ሊቀመንበር አቶ ሙሜ አዳም ተናግረዋል ።

ሌላኛው የለገ ኦዳ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ የሆነችው ወይዘሮ ፈጡማ አሜ ለድሬዳዋ ፖሊስ ሚድያ እንደገለጹት በወረዳው ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ አባላትና መላው ነዋሪዎች በጋራ በመተባበር ከበፊቱ በተሻለ መልኩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን ትናገራለች ።

የሁሉል ሞጆ እና የዋሄል ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪዎች በበኩላቸው ፖሊስ ብቻውን የአካባቢውን ሰላምና የህብረተሰቡን ደህንነት ማስጠበቅ አይችልም ያሉት ሲሆን ህብረተሰቡ ከፀጥታ አካላት ጎን ሆኖ በአካባቢው ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አስቀድሞ መከላከል እና የሰላም ጠንቅ የሆኑትን እንቅስቃሴዎች ነቅቶ በመጠበቅ ለአካባቢው ሰላም መስፈን ዘብ በመቆም ላይ መሆናቸውንና ይህንኑ አጠናክሮ እንደሚቀጥሉ ለድሬዳዋ ፖሊስ ሚድያ አስረድተዋል::

## < < በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የተመለከትነው ሰው ተኮር ስራ የሚደነቅ ነው > >

### ክቡር አቶ ዳንኤል ተሬሳ

### የስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ዴኤታ

የስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ዴኤታ ክቡር አቶ ዳንኤል ተሬሳን ጨምሮ የስራ ክህሎት ሚኒስቴር ከፍተኛ የልዑካን ቡድን የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለውጡን ተከትሎ ባለፉት አጭር አመታት የተገበራቸውን ስራዎች ተዘዋውረው ጎብኝተዋል፡፡

በጉብኝቱ ላይ የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የየስራ ክፍሉ ዳይሬክቶሬቶች ተገኝተዋል ።

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ተወካይ አዛዥ ረዳት ኮሚሽነር ጌታሁን አበራ በጉብኝቱ ወቅት እንደገለጹት የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ከለውጡ ወዲህ ቁርጠኛ አቋም ወስዶ ወደ ስራ በመግባቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ሊመጣ መቻሉን አብራርተዋል ፡፡

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በፖሊስ አመራር እና አባላት ዘንድ የነበሩ በርካታ ችግሮችን ተከታታይነት ባለው ስልጠና በማስተካከል ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በዚህም መሰረት የከተማውን ሰላም እና



ጸጥታ አስተማማኝ ማድረግ መቻሉን የጠቀሱት ረዳት ኮሚሽነር ጌታሁን አበራ በልማቱ ዘርፍም ከመንግስት ምንም አይነት በጀት ሳይመደብ በከተማው ባለሃብቶች ድጋፍ እና በፖሊስ አመራር እና አባላት ቁርጠኛ ተሳትፎ ስራዎች መሰራታቸውን ጨምረው ተናግረዋል ፡፡

ክቡር አቶ ዳንኤል ተሬሳ የስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር

ዴኤታ በበኩላቸው በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የተመለከቱት ሰው ተኮር ስራ የሚደነቅ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ብዙ ልምድ የሚወሰድባቸው ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡፡

የስራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ዴኤታን ጨምሮ የስራ ክህሎት ሚኒስቴር ከፍተኛ የልዑካን ቡድን የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ለውጡን ተከትሎ ባለፉት አጭር አመታት የተገበራቸውን ስራዎች ተዘዋውረው ከጎበኙ በኃላ እንደገለጹት በተሰሩ ስራዎች መደሰታቸውን ገልጸው፤ ከድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በርካታ ልምድ በበቂ ሁኔታ መቅሰማቸውን ተናግረዋል፡፡

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ “በ2022 በኢትየጵያ በላቀ ሞያዊ አገልግሎት ቀዳሚ የፖሊስ ተቋም ሆኖ ማየት” የሚል ርእይ ሰንቆ ወደ ስራ መግባቱ ይታወሳል ።

## በተደጋጋሚ ጊዜ ህይወት የማዳን ተግባር የፈፀመው የፖሊስ አመራር በባልደረቦቹ እውቅናና ምስጋና ተቸረው

ረ/ኢ/ር ፋሲል ካሳዬ ለፈፀመው የጀግንነት ተግባር የእውቅናና ምስጋና የምስክር ወረቀት ተበርክቶለታል።

በድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ዲቪዥን የስራ ባልደረባ የሆነው ረ/ኢ/ር ፋሲል ካሳዬ በከተማዋ ውስጥ በተለያየ ግዜ በሚያጋጥመው የሰው ሰራሽ ሆነ የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ከቡድን አባሎቹ ጋር ፈጥኖ በመድረስ የሰውን ህይወትና ንብረት በማዳን በተለያዩ ግዜያት ለገዛ ህይወቱ እንኳን ሳይሳሳ የሰዎችን ህይወት ሲያተርፍና ንብረቶችን ከውድመት ሲታደግ ስለነበረ ለፈፀመው የጀግንነት ተግባር የእሳትና ድንገተኛ አደጋ ዲቪዥን አመራርና አባላት የምስጋናና የእውቅና ምስክር ወረቀት ተበርክቶለታል ።

አመራሩም ይህንን ተግባር በመፈፀሙ እጅግ ከፍ ያለ ደስታ እንደሚሰማው ጠቅሶ ቃል ለገባለት ሙያ እስከ ህይወት መስዋዕትነት ሊከፍል ዝግጁ እንደሆነ በኩራት ገልጿል።


## የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በድሬዳዋ አስተዳደር ከከተማ እና ገጠር ቀበሌዎች ለተመለመሉ ወጣቶች መሰረታዊ የፖሊስ ስልጠና መስጠት ጀመረ

ለ14ኛ ጊዜ በሚካሄደው ስልጠና ቁጥራቸው 200 የሚሆኑ ምልምሎች በሁርሶ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ፖሊሳዊ ስልጠና እየተሰጣቸው ይገኛል ።

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ባወጣው የቅጥር ማስታወቂያ ከተመዘገቡት ቁጥራቸው በርከት ያሉ የአስተዳደሩ የከተማ እና የገጠር ቀበሌዎች የተውጣጡ ወጣቶች መካከል የተዘጋጀውን ፈተና እና ህክምና ያለፉ ቁጥራቸው ሁለት መቶ የሚሆኑትን ተቀብሎ ፖሊሳዊ ስልጠና እየሰጠ መሆኑ ታውቋል።

የድሬዳዋ ፖሊስ በቀጣይ ሊደርስበት ላስቀመጠው ራዕይ መሳካት ትልቁን ቦታ የሚይዘው እና ዋንኛው የሰው ኃይል በመሆኑ በተሻለ መልኩ በማሰልጠን ለህብረተሰቡ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ከመቼው ጊዜ በላይ እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ለ14ኛ ግዜ ወደ ተቋሙ የተቀላቀሉ ምልምሎች በማሰልጠኛ በሚኖራቸው ቆይታ በትምህርትና በአካል ብቃት የተሻለ ስብዕና ባለቤት ሆነው እንዲወጡ በትኩረት እየተሰራ መሆኑ ታውቋል።

የድሬደዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በሀገሪቱ ቀዳሚ የፖሊስ ተቋም ሆኖ እንዲወጣ በሰው ኃይል



፣በቴክኖሎጂ ፣በአሰራር ፣በግንኙነት ፣ በሎጀስቲክስ እና ፖሊሳዊ ስነ -ምግባር ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል ።

የድሬዳዋ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በ2022 በኢትዮጵያ በላቀ ሞያዊ አገልግሎት አንድ እርምጃ ቀዳሚ የፖሊስ ተቋም ለመገንባት ራዕይ አስቀምጦ እየተጋ ያለ ተቋም መሆኑ ይታወቃል ።




19ኛ ዓመት | ቁጥር 872 | ሳምንታዊ ዕትም | ረቡዕ - ሚይዚያ / 16 / 2016 ዓ.ም

## ድሬዳዋ ወደ ድል ተመልሷል !

በብሩክ ደስታ

በ22ኛ ሳምንት የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ድሬዳዋ ከተማ ሻሸመኔ ከተማን 1-0 በሆነ ውጤት በማሸነፍ የድሬዳዋ ቆይታውን በድል አጠናቋል።

ከ16 ተኛ ሳምንት ጀምሮ በድሬዳዋ ኢንተርናሽናል ስታዲየም የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ በደማቅ ሁኔታ ጅማሮን በማድረግ በመጨረሻው የ22 ኛ ሳምንት ኢትዮጲያ ንግድ ባንክ መሪነቱን ያሰፋበት እና የደረጃ ለውጥ ያስከተሉ ውጤቶችን አስመልክቶናል።

በድሬዳዋ ቆይታው ከፍተኛ ነጥብ ከሰበሰቡ ቡድኖች መሀል አንደኛው የሆነ ድሬዳዋ ከተማ ሻሸመኔን 1-0 በማሸነፍ ቆይታው በድል አጠናቋል።

በ21ኛው ሳምንት የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ ከወላይታ ዲቻ ጋር 1-1 በተለያየበት ጨዋታ ከተጠቀሙት አሰላለፍ የ አምስት ተጨዋቾች ለውጥ በማድረግ ወደ ሜዳ መግባት ችለዋል።

በመጀመሪያዎቹ አስር ደቂቃዎች ጫና ፈጥረው መጫወት የቻሉት ሻሸመኔዎች ግብ ቢያስቆጥሩም ከጨዋታ ውጪ በመሆኑ ተሽሮባቸዋል።

በአንፃሩ ድሬዳዋ ከተማ በአቤል አሰበ በሙኸዲን ሙሳ እና በካርሎስ ዳምጠው ተደጋጋሚ ሙከራ ቢያደርጉም ኳስ እና መረብን ሊያገናኙ አልቻሉም።

በመጀመሪያው 45 መጠናቀቂያ ደቂቃዎች ላይ ካርሎስ ዳምጠው ከሳጥን ውጪ ድንቅ ግብ በማስቆጠር ድሬዳዋ ከተማን መሪ ማድረግ ችሏል።



ከዕረፍት መልስ በአጠቃላይ የጨዋታ እንቅስቃሴ ተሽለው መቅረብ የቻሉት ሻሸመኔ ከተማዎች ተደጋጋሚ ጊዜ ሙከራ ቢያደርጉም በጨዋታው ጥሩ እንቅስቃሴ ማድረግ የቻለው የድሬዳዋ ከተማው ግብ ጠባቂው አብዩ ካሳዬ ኳሶቹን ማዳን ችሏል።

በሁለተኛው አጋማሽ የመጨረሻ አስራምስት ደቂቃዎች ብርቱካናማዎቹ ተጨማሪ ግብ ለማስቆጠር ተደጋጋሚ ሙከራ እና ጫና መፍጠር ቢችሉም ኳስ እና መረብን ማገናኘት አልቻሉም።

ጨዋታውም ተጨማሪ ግብ ሳያስተናግድ በድሬዳዋ ከተማ 1-0 አሸናፊነት ተጠናቋል።

ውጤቱን ተከትሎ ድሬዳዋ ከተማ 33 ነጥቦችን በመሰብሰብ 8ኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችሏል።

የኢትዮጲያ ፕሪሚየር ሊግ የድሬዳዋ ቆይታው በማጠናቀቅ ከአስር ቀናት ዕረፍት በኋላ በ23ተኛ ሳምንት በሀዋሳ ከተማ የሚቀጥል ይሆናል።

## ካፍ የክለብ ላይሰንሲንግ አውደ ጥናት በአራት ሀገራት ለማካሄድ ሲወስን ኢትዮጵያም እንድታዘጋጅ ተመርጣለች




የአፍሪካ እግርኳስ ኮንፌዴሬሽን (CAF) 54 አባል ሀገራትን ያካተተ አውደጥናት ለማካሄድ ዝግጅቱን መጀመሩን ሲያሳውቅ በሞሪታኒያ በሚጀምረው አውደጥናቱ በተለያዩ አራት ሀገራትም እንደሚቀጥል ሲታወቅ ሀገራችን ኢትዮጵያም አዘጋጅ ሆና መመረጧ ታውቋል። በዚህም

– ከዛሬ ሚያዚያ 14 ጀምሮ እስከ ዓርብ ሚያዚያ 18 በሞሪታኒያ

– ከሚያዚያ 21 እስከ ሚያዚያ 25 በአልጄሪያ

– ከሚያዚያ 30 እስከ ግንቦት 4 በኢትዮጵያ

– ከግንቦት 11 እስከ ግንቦት 15 በጋና አዘጋጅነት እንደሚደረግ ይፋ ሆኗል።

ኢትዮጵያ በምታዘጋጀው አውደ ጥናት

ኢትዮጵያ ኤርትራ ሶማሊያ ሲሼልስ ዛምቢያማላዊ ናሚቢያ ሞሪሽየስ ዚምባቡዌ ደቡብ ሱዳን ሱዳን ታንዛኒያ ሊቢያ ዩጋንዳ ሩዋንዳዛንዚባር ( ተጋባዥእንግዳ ) የሚካፈሉ ይሆናል።

**ምንጭ:(Cafonline.com)**

## ኖቲንግሀም በዳኛ በደል እንደ ተፈፀመበት ገለፀ !



ከሊጉ ላለመውረድ ከፍተኛ ፉክክር ውስጥ የሚገኘው ኖቲንግሀም ፎረስት በ34ተኛ ሳምንት የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ በኤቨርተን 2-0 በተሸነፈበት ጨዋታ በዳኛ በደል እንደተፈፀመበት ገልጿል።

በጨዋታው ሶስት ፍፁም ቅጣት ምቶች ተከልክለናል የሚለው ኖቲንግሀም ፎረስት በመግለጫው ተቀባይነት የሌለው ውሳኔ ነው አሳዝኖናል ሲልም ገልጿል።

የቫር ዳኛው ከእኛ ጋር ላለመውረድ የሚፎካከረው ሉተን ታውን ደጋፊ መሆናቸውን ቀድመን ለዳኞች ኮምቴ ብናሳውቅም ሰሚ አጥተን ሳይቀየሩ ቀርተው በደል ፈፅመውብናል ሲል ክለቡ ቅሬታውን አቅርቧል።

በውድድር አመቱ ውስጥ በዳኞች ውሳኔ ትእግስታችን ተፈትኗል የሚሉት ኖቲንግሀሞች አሁን ግን ሌሎች ህጋዊ አማራጮችን ለማየት ተገደናል ብለዋል።

ኖቲንግሀም ፎረስት በዘንድሮ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ባደረጋቸው 34 ጨዋታዎች 26 ነጥቦችን በመሰብሰብ ከወራጅ ቀጠናው በአንድ ነጥብ ከፍ ብሎ 17ተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።

## በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው የቦክስ ሻምፒዮና በኢትዮጵያ ጥሩ ውጤት ተመዘገበ




ወደ ገጽ 10 ዞሯል

## የአምናው እምባ እየታበሰ ነው



ወደ ገጽ 10 ዞሯል